ቅፅ ፩ ቊጥር ፭ ኅዳር ፲፱፻፹፭

ጩኸታችን መልሶ እንዳያሳፍረን

የደመወዝ ጭማሪና
የጉምሩክ ቀረጡ ጉዳይ

ስለ ስም ማጥፋትና ተጠያቂነት

"የኛ መነጣጠል ለጠላት መመቸት ነው።"

ዘርዓይ ደረስ

"......ይህች ቀውጢ ጊዜ አልፋ የሰላም፣ የፍቅ
ርና የመተሳሰብ ጊዜ እንደሚመጣ አልጠራጠርም።"

ኰ/ል ጎሹ ወልዴ

ከታሪካችን

የዘርዓይ ደረስ መልዕክት

(1908-1937)

(ከአካሉ ወ/ማርያም)

"ዛሬ ከኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን ጐን ተ ሰልፈን የፋሽስት ኢጣሊያን ጦር ድል በመንሳት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የአገራችንን አንድነትና ሉዓላዊነት ማረጋገጥ አለብን። ንጉሠ-ነገሥት አፄ ቴዎድሮስ እጄን አልሰጥም አገሬን አላስደፍ ርም ብለው በገዛ ሽጉጣቸው ሕይወታቸውን አሳልፉ። አፄ ዮሐንስ ዳር ድንበር ለማስጠበቅ ባደረጉት ጦርነት መተማ ላይ ወደቁ። ጀግናው ራስ አሉላ የምዕዋን በር አላሳልፍም በማለት የጣሊያንን ጦር ወደመጣበት መለሱ። ትላንት በዚህ ሁኔታ ያለፉ አባቶቻችንን አርአያነት ተከትለን ይህችን አገር ከታሪክ ጉድፍ ባናድናት የእነሱ አጥንት ይወጋ ናል፣ አፅማቸው ይሞግተናል" ያለን ጀግናው ዘር ዓይ ደረስ ነበር።

ዘርዓይ ደረስ ገና ከልጅነቱ ጀምሮ የጣሊ ያን መንግስት አገዛዛ ያስመረረው፤ የትውልድ ሀገ ሩ የሆነችው የዛሬዋ ኤርትራ ከእናት አገሯ ኢት ዮጵያ በሃይል ተነጥቃ በኰሎኒያሊስቶች ሥር በመው ደቋ ቁጭቱ ከለት ዕለት እየጋመ የመጣ እንደነበ ርም ታሪክ ይመሰክራል።

በተለይም ፋሽስት ኢጣሊያ መላውን የኢት ዮጵያ ግዛት ለመቆጣጠር ጦር በሰበቀችበት ወቅት፤ "እምቢ ለሃገሬ፣ እምቢ ለነፃነቴ በማለት" በዱር በገደሉ በአርበኝነት ተሰማርተው ከነበሩት የመሃል ኢትዮጵያ ወገኖቻቸው ጐን የኤርትራ ልጆች እንዲ ሰለፉ ከፍተኛ ግፊት አድርጓል። ይህ በኢትዮጵያ ዊነቱ ሙሉ እምነት የነበረው ወጣት፣ሮማ በአስተ ርጓሚነት በሄደበት ወቅት የጓደኛውን ባንዳ መሆን በሰማ ጊዜ ለወንድሙ ተስፋዕዮን የፃፈለት ደብዳቤ ይህንኑ እውነት ያረጋግጣል። የደብዳቤው ሙሉ ቃል ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል፤

"ማንኛውም ፍጡር ወላጁን መስሎ ነው የሚ ወጣው፤ ለምሳሌ ዝንጀሮ ጦጣን መውለድ አትችልም። ጦጣም ነብርን ወይም አነርን መውለድ አይቻላትም። ሌላውም ፍጡር ሁሉ እንደዚሁ ነው።

አባቶቻችን በምሳሌ ሲሰድቡ 'መሬት ሲያ ረጅ መጭ ያበቅላል' ይላሉ እነሱ በኩራትና በክ ብር በደማቸውና በአጥንታቸው የገነቡትን ነፃነት እኛ ዛሬ እንሻሻጥበታለን፤ ያሳዝናል፤ ወይ አል ቀደምን ወይንም ወደኋላ አልቀረን፤ በመሃል ቤት ተፈጥረን በመንፈስ እንሰቃያለን፤ ገብረዓብ የሰ ራኝን ስምተህ አንተም ስለ ጉዳዩ ጽፈኸልኛል፤ ሃዘኑ የኔ ብቻ ሳይሆን እገሩንና ወገኑን ለሚወድ ሁሉ ይተርፈዋል፤ እኛ ዛሬ ልጆች አይደለንም፤ ብሔራዊ ፍቅርና አንድነታችንን ማጥናት አለብን፤ ለዕለት ሆዳችን መለዋወጥ የለብንም፤ ጠላቶቻችንም የኛን መነጣጠል ስለሆነ የሚሹት ይኸው ያዘላቸው። እኔ ወንድሜ ወገኔ ነው ብዬ ለአንድነታችን የሚጠ ቅም ሃሳብ ብዕፍለት እስከዚህ አሳልፎ እንዴት

ይሰጠኛል? ለመሆኑ ሌላ ከበድ ያለ ምስጢር ብፅፍ ለት ኖሮ ያለፍርድ አሰቅሎኝ ነበር ማለት አይደለ ምን? ያሳዝናል፤ በእውነቱ እልሃለሁ፤ ዛሬ እኛ ተማርን ብለን ከምንመፃደቀው ወጣቶች ይልቅ ከኛ በፊትም ሆነ አሁን በቅን ላገራቸው የሚሰየፉት መሃይምኖች በጣም ይበልጡናል።

አሁን ለምሳሌ ከሃማሴንና ከጠቅላላው ኤር ትራ ግዛት ከኢጣሊያ እያመለጡ ከአርበኞች ጋር ተቀላቅለው ለክብራቸውና ለነፃነታቸው በዱር በገ ደል ስቃይን የሚቀበሉት ህዝቦች ቁጥራቸው ብዙ ነው። የናቴን መሰቃየት እያሰብኩ ለስም የሚሆን ነገር ሳላትርፍላት እያልኩ እንጂ ሆዴ ፍፁም እየ በረደው ለመኖር አልመርጥም ነበር። ስለዚህም አ ቅጣኝና አፍጣኝ እመዳሮው ላይ እንገናኝ እንደሚባ ለው አነጋገር ሁሉ እኔ ለማን እንደማስብ እነሱም ለማን እንደሚያስቡ አንድ ቀን መለየቱ የማይቀር ነው። ለማንኛውም በቅርብ እመጣለሁ።

ይኸውና ልመለስ እያልኩ ስለምን ብዙ ጊዜ ሆነኝ። አየሩ አልተስማማኝምና ወደ አገሬ ሄጀ ትንሽ አየር ልለውጥ ብዬ አለቃዬን በመለመን ላይ ነኝ።

እኔና ገብረ-አብ ዓይን ለአይን መተያየታ ችን አይቀርም። በኢትዮጵያ ላይ በአይን-ሀሊናህ ሆነህ የምታየው ግፍ ቃላቶች አይዘረዝሩትም። ከ

ሁሉም የሚገነደኝ ከመሀል ኢትዮጵያ ድረስ እየመጡ በመገናኛውና በሆገራቸው ላይ የሚቀላምዱትን የኢጣሊያ ደጃዝማቾች ስለማና ላይ ነው። እኔ በነገር ብቻ ሳምባዬ አረረ አሁንስ በጣም ነው የመረረኝ።

ከነሱ የማገኘው ክብርና ፀጋ ሁሉ ሰውነቱን እንደ ዶሮ ቅንቅን ሲበላኝ ነው የሚያድረው፤ ለማንኛውም ሃሳቤ እንደተሳካልኝ እመጣለሁ፤ ያቺንም ጕራዴ እገኝቻታለሁ፤ ግን እጇ አልገባችም። ስለጕራዲዋ ስንገርህ እንደምትደነግጥ ይሰማኛል፤ ግን በልዩ ዘዴ እመጣታለሁ፤ አትስጋ። ይህንማ ካላደረግሁ ዉርሶ የኢጣሊያ መሣሪያ ነኝ ማለት ነው።

በል እንግዲህ ለገብረ-እብ ከእንግዲህ እስላምና ክርስቲያን መሆናችንን እንዲያውቀው ንገረው፤ ባልሊኪም ሁኔታውን እንደሚነግረው አውቃለሁ።

ግን እኔ ስመጣ ወደኔ ተለጥፎ ለመቀላመድ እንደይችል አስጠንቅቀው። በኋላ ጉድ እንዳይፈላበት። ከአሁን በኋላ እንደዚህ ባሉት ሃማሴን ጕሳዎች ላይ ሌላ እርምጃ ነው የምወስደው። እናታችን እንዳትሰጋ ስለማንኛውም ነገር አትንገራት፤ በል ደህና ሁን።"

ዘርዓይ ደረሰ በ፲/፲፪/፲፱፻፳፱

ኑሮው ከማንም በታች ሳይሆን፤ ከጣሊያን መንግስት ያን ያህል ከበሬታ አግኝቶ በአስተርጓሚነት ሮማ የነበረው ወጣት ለመሆኑ መቼና እንዴት ተወለደ? አስተዳደጉስ ምን ይመስል ነበር? ለአገር አንድነትና ነፃነት ያነሳሳው ምክንያት ምንድነው?....ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በስፋት መነጋገር ይቻላል። ሆኖም ባለብን የቦታ እጥረት ምክንያት ገረፍ ገረፍ አድርገን ለማለፍ እንሞክራለን። ለዚያውስ ለትምህረት ካለው ከባለ ታሪክ ገድል ውስጥ አንዱ ብቻ ይበቃ የለም!!

የዘርዓይ ደረሰ የትውልድ ሥፍራ በዛሬዋ የኤርትራክፍለሀገር በሰራዬ አውራጃ አዲሃይስ ከተባለች ቀበሌ በ1908 ዓ.ም. ነው። በልጅነቱ ዘመን አባቱን ያጣው ዘርዓይ ደረሰ ከሌሎች ወንድሞቹና እህቶቹ ጋር የእናቱ እንክብካቤ አልተለየውም። የተወለደበት ዘመን የጣሊያን መንግስት የኤርትራን ግዛት ከእናት ሃገሯ ኢትዮጵያ ከፍላ (ቆርሳ) በመውሰድ ታስተዳድር የነበረበት በመሆኑ፤ ይህንን የጣሊያን የመስፋፋት ፖሊሲ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው የካቶሊክ የወንጌል ሰባኪዎች በየቦታው ት/ቤት በመክፈት የክልሉን ወጣት ስነ-ልቦና የሰለቡበት ወቅትም ነበር ቢባል ግነት የለውም። የዚህ ዓይነቱ ስነ-ልቦና ሰለባ ዕጣ ከደረሳቸው ወጣቶች አንዱ ጀግናው ዘርዓይ ደረሰ ነበር።

ገና በጨቅላነቱ ወቅት የካቶሊክ ሚሲዮን ት/ቤት የገባው ዘርዓይ ትምህርቱን በሚገባ ይከታተል እንጂ፤ የሚማረው የወንጌል ትመህርት የጣሊያን መንግስት በሕዝቡ ላይ ከሚያደርስበት በደል ጋር ፈፅሞ የማይጣጣም ሆኖ አገኘው። በተለይም ጣሊያን መላውን ኢትዮጵያ በተቆጣጠረችብት ወቅት በመፈፀም ላይ ከነበርችው ደባ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርስ የሆኑት የይሁዳ አንበሳና የአክሱም ሃውልት ተግዞ መሄድ ይበልጥ ራሱን እንዲፈልግ ገፋፋው።

ራሱን በመፈለጉ ጥረት የኢትዮጵያን ታሪክ መከታተል ሥራዬ ብሎ የተያየዘው ጀግና የአማርኛን ቋንቋ ጠንቅቆ ለማወቅ ጊዜም አልፈጀበትም ነበር። በቋንቋው እየታገዘ የእኔ ማንኘነቱን ጥያቄ "ኢትዮጵያዊ" በሚለው ጥቅል ስም ውስጥ ያገኘው ዘርዓይ ደረስ፤ በትምህርቱ በነበረው የላቀ ውጤት ኩረም በተባለው ስፍራ ሄዶ እንዲያስተምር ተወሰነ።

"እናቱን ያገባ ሁሉ አባቴ ነው" የሚለው አባባል የደካሞችና የሰነፎች እምነት ነው። በባዕድ ኃይል መገዛትም ከዚህ ተነጥሎ ሊታይ አይገባውም በማለት ለነፃነትና ለአገር አንድነት ቆርጦ የተነሳው ወጣት በኩረም ተማሪዎቹን ሰብስቦ ከሚሰጠው ትምህርት በላይ ቅስቀሳው ያይል ነበር። ተማሪዎቹን ሰብስቦ እያንዳንዳቸው በግፈኛው መንግስት የደረሰባቸውን በደል ይጠይቃል። ከተማሪዎቹ ከሚሰነዘር መልስ በመነሳት፤

"ምናልባት በእግዜአብሔር ሃይልና ፈቃድ ይህ ግፈኛ መንግስት የተደመሰሰልን እንደሆን የነፃነትን ያንድነትን ጥቅም ማወቅና መገንዘብ የኛ ፋንታ ነው። ይኸውላችሁ ነፃነት የሌለው ህዝብ ለመታረድ ወደቄራ እንደሚነዳ ከብት ነው። ነፃነት ቢኖር ኖር ያንተም እናትና እህት በእሳት ተኩማትረው ባልቀሩ፤ በገመድ ታስረው በሳንጃ ተወግተው ወደ ገደል ባልተጣሉ ነበር። የነፃነትን ያንድነትን ዋጋ ለይቶ ማወቂያችሁ ጊዜው አሁን ነው። ምክንያቱም ሥራው ራሱ ሊያስተምራችሁ ይችላልና ነው። ነፃነት ከማንኛውም ዕንቁና ወርቅ የበለጠ ጥራትና ክብር ያለው ሌላ ተመጣጣኝ ነገር የማይገኝለት ሀብት ስለሆነ አበክራችሁ እጥኑት እወቁትም" በማለት በዚያ የእሳት ዘመን ያደርግ በነበረው ቅስቀሳ የነፃነት እንቅስቃሴ መሥራች መምህር እንደነበር ከታሪኩ መረዳት ይቻላል።

ጥናቱን ባለማቋረጥ ስለኢትዮጵያ ማንነት ይበልጥ ባወቀ ቁጥርም የኢጣሊያንን የአገዛዝ ምስጢር እየፈለፈለ ይፋ ከማድረግ የተቆጠበበት ጊዜ አልነበረም። በግል እያዘጋጀ ይበትን የነበረው ድብቅ ፅሁፍ ለዚህ ዓይነቱ እንቅስቃው ምስክር ሊሆን ይችላል። ከነዚህ ድብቅ ፅሁፎቹ አንዱን እንኳን ብንመለከት፤

"እኛ ኢትዮጵያዊያን እንጂ ጣሊያናዊ አይ

ደለንም። በኢትዮጵያዊነታችን ብዙ የሚያኮራን ታሪክ አለን። ዓለምን የሚያስቀና ዘርና ሃገር አለን። የኛ መንጣጠል ግን ለጠላት መመቸት ነው። በራሱ ታሪክ፣ በራሱ ሃገር የማይተማመን ዜጋ በጠፈር ላይ የተበተነ ዱቄት ይመስላል። መማር፣ ማንበብና፣ መፃፍ በይበልጥ አገርንና ወገንን ለመውደድ እንዲያበቃ እንጂ አጉል ጥራዝ ነጠቅ ሆነን ላገራችን ሸክምና በሽታ ልንሆንባት አይገባም" በማለት በወቅቱ የነበሩትን ጓደኞቹንና ወጣቶችን ልብ የሚቀሰቅስበት እንደነበር መረዳት አያዳግተንም።

የዘርዓይ ደረስ ትግል በድብቅ ፅሁፍ የተገታ አልነበረም። በአንድ ወቅት ይፋዊ መልክ ይዞም ነበር። ወንጌላዊያን የተጠቀሙበትን መንገድ እሱም በነርሱ ላይ ተጠቅሞባቸዋል። ኢትዮጵያ በጣላቷ እጅ ከፉኛ በመውደቋ ምክንያት በፀሎትና በመንፈስ ከኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻችን ጉን እንሰለፍ በሚል ዓላማ ለተመሠረተው "ገብረ-ሚካኤላዊያን" ማህበር በፕሬዝዳንትነት ተመርጦ አገልግሏል።

በነዚህና መሰል የትግል ስልቶች ጠላትን በአገር ውስጥ ዲፕሎማሲ በተሞላው መልክ ሲፋለም የቆየው ወጣት ጀግና ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ በአዕምሮው ውስጥ እሳት የጫረበት የአሉላ አባ ነጋ ጉራዴ እንደነበር ይነገራል።

በሐምሌ ወር 1928 ዓ.ም.የመቀሌ ገዢ የነበረው ኮማንዳቶሬ እስኩድራ የተባለው ፋሽስት ወደ ሮማ ለመሻገር ከመቀሌ ወደ አስመራ በመጣበት ወቅት አንድ ጉራዴ እንደሻምላ በእጁ ይዞ ሲንጉራደድ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ይመለከተዋል። ጠጋ በማለት አዋቂዎችን ስለጉራዴው ይጠይቃል። ጉራዴው የአሉላ አባ-ነጋ እንደነበርና፤ ዶጋሊ ላይ ጣሊያንን ድል የነሳው በዚህ ጉራዴ እንደሆነ ይነገረዋል። አእምሮው ይረበሻል። ወዲያው ስለገጠመው ሁኔታና ጉራዴውን ሊያገኝ ስለሚችልበት ሁኔታ ወንድሙን ያማክራል። ወንድሙ ግን ለነገሩ እምብዛም ክብደት አልሰጠውም። በዚህ የተበሳጨው ዘርዓይ፤

"ብረት ሁሉ ብረት አለመሆኑን ከድንጋይ እንኳን የተመረጠ ድንጋይ መኖሩን አትዘንጋ። ጣሊያኖች ከጉራዴ ለይተው ሮማ የወሰዱት የተለየች ስለሆነችና ታሪከኛ መሆኗን አውቀው ነው። ሁልጊዜም አንድ አገር በሌላው ሲወረር ከተወረረችው አገር ውስጥ አስቀድሞ የሚሄድ የታሪክ ዕቃ ነው። ይኸውም ታሪክን ለማጥፋት ከሚታሰበው ብርቱ ባለጋራነት የተነሳ መሆኑን ልታውቀው ይገባል። ስለዚህ ነው የታሪክ መታሰቢያ ከሌለን ታሪካችን ይጠፋል የምልህ" በማለት አስረዳው። ግና ያሰበውን ሊፈፅም፤ ኢትዮጵያን የነፃነትና ጀግንነት ታሪክ በዓለም መዝገብ ደግሞ ሊያፅፍ ያበቃው ወቅት ደረሰ። አጋጣሚው እንዲህ ነበር። በሮማ ውስጥ በአስተርጓሚነት የሚያገለግል አንድ ሰው በማስፈለጉ ለዚህ ብቃት ያለው ዘርዓይ ደረስ መሆኑ በቀድሞ አስተማሪዎቹ ታምኖበት ተላከ። ከሄደበት ጊዜ ጀምሮ ከአገር ውስጥ አርበኞች ጋር ያለውን ግንኙነት አላቋረጠም። በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደ አገሩ ተመልሶ ከወገኖቹ ጋር በመሆን ቆራጥ ተጋድሎ ለማድረግ ከማሰብ የቦዘነበትም ጊዜ አልነበረም። ሆኖም ያዚያች ጉራዴ አለመመለስ ማለት ታሪክን መሸጥ ማለት ነው እያለ እራሱን ያበረታታ ነበር። በመጨረሻም ለእረፍት ወደ አገሩ እንዲመለስ ሲፈቀድለት በጠየቀው ጥያቄ መሠረት የአሉላ አባ-ነጋ ጉራዴ ለኮማንዳቶሬው መልሶ እግረ-መንገዱን እንዲያደርስለት ከስምምነት ላይ ተደረሰ።

ያሰበው የተሳካለት ዘርዓይ ደረስ እቃውን ባቡር ለማስጫን በዝግጅት ላይ እንዳለ ጉራዴውን እንደታጠቀ የይሁዳ አንበሳን ለመሰናበት ወደ ፒያሣ (ሮማ) ወጣ። በዚያ እንደደረሰ አንበሳው ላይ የተኩላ ምስል ተቀምጦ ተመለከተ። ጠጋ በማለት በላዩ ላይ የተፃፈውን ጥቅስ አየ። ጥቅሱም፤ "ልጆችሽ የይሁዳ አንበሳ እየተባለ በቃለ-አጋኖ ሲወራለት የነበረውን ከሃገሩ እንደፍየል ጭራውን ጠምዘው አምጥተው ከግርሽ ሥር ያስገዱታል" ይላል። በአካባቢው የተሰበሰበውም ህዝብ እየጮኸና በየተራ ከአንበሳው ላይ እየወጣ "ብላ የተራብከው አንበሳ ከድህነት አመጣንህ ምግብ ሞልቷል! ሆድህን እየሞላህ ማገገም አለብህ" በማለት ዳቦ በአፉ ውስጥ እየጨመሩ ይሳለቁበታል። ጀግናው ግን ሁኔታውን በቁጣ ያስተውላል።

ወዲያው ሳይታሰብ ከተማዋን ሲቆጣጠር የነበረው ማርሻል ማርዴ በሦስት ሻምላ የያዙ አጃቢዎቹ ታጅቦ ብቅ አለ። ዘርዓይ ደረስን በመጥራት አንተ እንድታይ ማን ፈቀደልህ አለው። ህዝብ የሚያየውን እንዴት አላይም በማለት መለሰ። .ምን ያደርግልሃል ከእንግዲህ አንበሳ የሚባል የለም ይልቅስ ለእመቤቲቱ ተኩላ ስገድ አለው። ጀግናው ከቁጥጥሩ ውጪ ሆነ። በአካባቢው ያለውን ሰው ሁሉ በጉራዴው አጨደ። በመጨረሻም ማርሻል ማርዴን ለአንበሳው እንዲሰግድ ካደረገው በኋላ አንበሳው ስር ቆራርጦ በመጣል፤ አንበሳውን ያሻሽ ጀመር።

የሕዝቡ ጩኸት ዳር ከዳር አስተጋባ። ከመንግስት አዋጅ ተነገረ። የአዋጁም መንፈስ፤ "ኢትዮጵያ ጠላታችን ከተማችንን ሰብራ ገብታለችና መሣሪያ ያለህ በመሣሪያህ የሌለህ ከመጋዘንህ እያወጣህ ለነፃነትህና ለክብርህ ቶሎ ገብተህ ተከላከል....." የሚል ነበር። በዚህ መሠረት ህዝቡ ተኩሱን አቀለጠው። እርስ በርስ ተፋጀ። ከብዙ የፋሽስት ኢጣሊያኖች ዕልቂት በኋላ ግን እግሩን በጥይት ተመትቶ የተያዘው ጠላት ብቸኛውና ኢትዮጵያዊው ጀግና ዘርዓይ ደረስ ነበር። በዘርዓይ ደረስ የደረሰባቸውን ውርደት ለመሸፈን እብድ ነው በማለት አስወሩ። እሱ ግን እብድ አለመሆኑን በተደጋጋሚ አስረዳ። እብድም እንኳን ቢባል ያሳባደው የኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት እንደሆነ ለመግለፅ ሞከረ። ብቻውን ሆኖ ሰሚ አጣ

-(ወደ ገፅ 47 ይዞራል)

ኰ/ል ጉሹ ወልዴ በኤርትራ ሊደረግ የታቀደውን ሕዝበ-ውሳኔ በተመለከተ

ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያስተላለፉት መልዕክት

የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን)

ጥቅምት 20 ቀን 1985 ዓ.ም.

ለክቡር ሚስተር ፍሎሬይን ሬንክል
በተባበሩት መንግስታት ድርጅት 47ኛው ጉባኤ 3ኛ ኮሚቴ
ሊቀመንበር

ክቡር ሚስተር ሬንክል:

ይህን ደብዳቤ የፃፍኩልዎት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በኤርትራ-ኢትዮጵያ ሊደረግ የታቀደውን ሕዝበ-ውሳኔ በሚመለከት ያቀረቡትን ዘገባ (Doc A/47/544) በመመርኮዝ ምላሽ ለመስጠት ነው። በዋና ፀሐፊው ጥያቄ መሠረት በሕዝበ-ውሳኔው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጣልቃ ገብነት በርካታ ህጋዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን ማስነሳቱ አይቀርም። እነኚህም መሠረታዊና አግባብ ያላቸው ህጋዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች በዚህ ኮሚቴ አማካኝነት በግልፅና ለሕዝብ ይፋ በሆነ መልካቸው ተነስተው ለውይይት መቅረብ ይኖርባቸዋል። ለዚህና ለመሳሰሉት ጉዳዮች መድረክ ለማግኘት የርስዎን ትብብር እንጠይቃለን። ይህን አቤቱታችንንም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወገኖችና የኮሚቴ አባላት ሁሉ እንደሚያስተላልፉልን ባለሙሉ ተስፋ ነን። ከዚህም በላይ በውይይት መድረኩ ላይ የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ ህጋዊ ዕውቅናና ውክልና ያለው የአፋር ህዝብ ተወካዮችና ማናቸውም በውይይት መድረኩ ለመሳተፍ ፍቃደኛ የሆኑ ፓርቲዎች ሁሉ እንደሚጋበዙና እንደሚሳተፉ በማመን ነው።

ክቡር ሊቀመንበር:

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ በኤርትራ ሊካሄድ በታሰበው ሕዝበ-ውሳኔ ባቀረቡት ዘገባ ላይ ያለንን ተቃውሞ እንድንገልፅ ይፈቀድልን።

በመሠረቱ በዋና ፀሐፊው የቀረበው ዘገባ በተዛቡ መረጃዎች የተሞላ ብቻ ሳይሆን በትክክል ሊገናዘቡ በማይችሉ ጭብጦችና ቁልጭ ብለው በሚታዩ ስህተቶች የተቀመረ ሀተታ ነው። ከዚያም በላይ ዘገባው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ላይ ስለሚያደርገው ጣልቃ-ገብነት አንድም አሳማኝ ነጥብ ሊያቀርብ አለመቻሉ ጥርጣሬአችንን ይበልጥ አጉልቶታል።
ቀጥለንም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ዋና ፀሐፊው ባቀረቡት ዘገባ ላይ የታዩትን ጉልህ ስህተቶችና አንዳንድ ግድፈቶች ለጉባኤው ለማቅረብ እንወዳለን። ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን ሁሉ "የራስን ዕድል በራስ መወሰን" መርሆ ብንደግፍም ኤርትራን በሚመለከት ግን የታዩትን እንከኖችና ጉድለቶች ከዚህ እንደሚከተለው በግልፅ እናቀርባለን።

1.ቀደም ብሎ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኤርትራን ጉዳይ በሰፊው አይቶና መርምሮ በፌዴራል አስተዳደር ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል {GOAR 390 V 1950} አድርጓል። በዚህም የኤርትራ ሕዝብ የራስን ዕድል በራስ መወሰን መብት ተጠቅሞ ድምፁን ሰጥቶ ከኢትዮጵያውያን ጋር ለመኖር ያለውን ፅኑ ፍላጐት በድምፁ አረጋግጧል። ተግባራዊም ሆኗል። ዛሬ ከ42 ዓመታት በኋላ ነፃ፣ ሉዓላዊነቷ የተጠበቀና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መርሆዎች የምትገዛ አንዲት የድርጅቱ መስራች ሀገር በውስጥ ጉዳይዋ ጣልቃ መግባት ምንም ህጋዊ መሠረት የለውም። የኤርትራ ህዝበ-ውሳኔ አስፈፃሚ ኮሚሽን አለም-አቀፍ ዕውቅናን ባላገኘው ድርጅት በህዝባዊ ግንባር አርነት ኤርትራ የተቋቋመ ነው። ትዕዛዙም ሆነ ቁጥጥሩ በዚሁ ግምባር ነው። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በዚህ ኮሚሽን ስለተጋበዘ ብቻ ከዘመናት በፊት በብርቱ ጥረትና ክትትል እልባት ያገኘን ጉዳይ እንደገና ለማየት መብቱም ሆነ ስልጣኑም አይደለም።

2.በሰኔ ወር የተካሄደው የሰላምና ዲሞክራሲ ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ "የኤርትራን ህዝብ የራስን ዕድል በራስ መወሰን መብት" ሙሉ በሙሉ እንደሚደግፍ ይፋ አድርጓል። በመሠረቱ ጉባኤው ሕዝበ-ውሳኔ ይደረግ/አይደረግ ለማለት የሚችልበት ህጋዊ ውክልናም ሆነ እውቅና የለውም። መብትና ሥልጣንም የለውም። በወቅቱ የተሰባሰቡት የጉባኤው ተሳታፊዎች ለሀገሪቱ የግዛት አንድነት እንዲመክሩ፣ እንዲከራከሩና

እንዲዘከሩ የተሰጣቸው አንዳችም ህገባዊ ውክልና አልነበረም። ጉባኤው የኢትዮጵያ እንደራሴዎች (ተወካዮች) ወይም ብሔራዊ ስብሰባ አልነበረም። በኢትዮጵያ እውነተኛ ልጆች ትክክለኛ ውክልና ያገኘ አይደለም። የጉባኤው ተሳታፊዎችም በዘፈቀደ የተመለመሉ ወይም በአብዛኛው ለኢሕአዴግ ጥቅም ሲባል ወዲያውኑ የተፈጠሩ የፖለቲካ ወይም የጉሣ ድርጅቶች ስብስብ ነበር ማለት ይቻላል። በመሆኑም በኢትዮጵያ የግዛት አንድነትም ይሁን በሌላ አብይ ርዕሶች ላይ የሚያደርጋቸው ውሳኔዎች ሆኑ እውቅናዎች በዜጐቿ ተቀባይነት እንደማይኖራቸው ልናስገንዝብ እንወዳለን።

3.የሽግግር መንግስቱ በህዝብ ፍላጐትና ሙሉ ድጋፍ በነፃና ዲሞክራሲያዊ ሂደት ያልተመሰረተ ስለሆነ የሀገሪቷን የወደፊት እድል ሊወስን ሥልጣን የለውም። መንግስቱ ጊዜያዊና የሽግግር ወቅት በመሆኑም የሥልጣን ገደቡም ውሱን ነው። በዚህ ስልጣኑም ፀንቶ የኖረውን የኢትዮጵያ አንድነት ለማፈራረስ የሚያደርጋቸው ስምምነቶች ተቀባይነት አይኖራቸውም። ከዚህም በላይ ከህገባዊ ግንባር አርነት ኤርትራ ጐን ለጐን ሲዋጋ የኖረው ኢህአዴግ የሚያደርገው የሀገር መበታተን ልዩ ሚና የህዝብ እምነትና ድጋፍ ያሳጣው ስለሆነ ሀገሪቱን በሚመለከት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ህዝቡን ወክሎ መናገር እንደማይችል በግልፅ ልናሳውቅ እንወዳለን።

4.ምንም እንኳን በዋና ፀሐፊው የቀረበው ዘገባ ከመረጃ እጥረት ሳቢያ በአካባቢው እየተካሄዱ ያሉትን የፖለቲካ ውጥረቶችና ስነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ ባያካትትም በግልፅ የሚታዩ ክስተቶች እንዳሉ መካድ ያስቸግራል። በኤርትራ ውስጥ በአፋር ነፃ አውጪ ግንባርና በህግሐኤ መሀከል ከፍተኛ ፍጥጫና ውጥረት አለ። በተቃራኒው የተዘገበው ዘገባ በኤርትራ ውስጥ ሰላም የሰፈነ መሆኑን ሲሆን ይህም በህዝቦች የዕለት-በዕለት የፀጥታ ወይም ደህንነት ላይ የሰፈነውን ስጋት ገሸሽ በማድረግ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ለማሳሳትና የተወሰነ ቡድን ዓላማን፣ ፍላጐትና የቆየ ምኞት ለማርካት ሆን ተብሎ የተቀናበረ ድርጊት ነው።

5.የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቡድን ህዝበ-ውሳኔውን እንዲከታተል ይደረግ ዘንድ በዋና ፀሐፊው የተሰነዘረው አስተያየት መሠረቱን የሳተ ከመሆኑም ባሻገር ቅድመ ውሳኔዎች ሳይሟሉና ማንስ ለዚህ ውሳኔ ድምፅ ህጋዊነት ይኖረዋል? መስፈርቶቹንም የሚያሟሉት ህጋዊ ድምፅ-ሰጪዎች የትኞቹ ወገኖች ናቸው? ወዘተ ለሚሉት አወዛጋቢ ጥያቄዎች መፍትሄ ሳይነድፍ የተሰነዘረ ሀሳብ ስለሆነ በጥንቃቄ እንዲታይ እንጠይቃለን። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ መ/ቤት አማካኝነት በሱዳን የሚገኙት የኤርትራ ተወላጅ ስደተኞች ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ለህዝበ-ውሳኔው ድምፅ እንዲሰጡ ያስተላለፈውን ውሳኔ ህግሐኤ ውድቅ አድርጐታል። በነበረው የሕዝቦች መተሳሰር፣ መቀራረብና አብሮ መኖር ባህል ከኤርትራ ተወላጆች ተጋብተው የተዋለዱ ሌሎች ወገኖች "ዘርን ማጥራት" በሚለው የህግሐኤ መመሪያ ከክልሉ መባረራቸው ይታወቃል። በሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች ተሠራጭተው የሚገኙ በርካታ ኤርትራውያን በድምፀ-ውሳኔው ላይ ምንም አይነት ተሳትፎና የድምፅ መስጠት መብት እንደሌላቸው በይፋ ተነግሯል። እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ-ህዝቡ ምንም ይሁን ምን ቃል መተንፈስ እንደማይችል ከወዲሁ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየተነገረው ነው። የሀገሪቱን የወደፊት እድል፣ የዜጐቹን መብትና የወደፊቱ ትውልድ ዕጣ-ፈንታ ለመወሰን መብት የለህም እየተባለ ነው። ይህ ሁሉ ድርጊት እየተከሰተ ሳለ ዋና ፀሐፊው ያቀረቡት አስተያየት(ሃሣብ) የመምረጥ መብት ያላቸውን በግልፅ ያላስቀመጠ ስለሆነ ጉድለት ይታይበታል። ይህም ጉድለት ህዝበ-ውሳኔውን ስንካላ እንደሚያደርገውና ውጤቱም ስነ-ልቦናዊም ሆነ ህጋዊነቱ አጠያያቂ እንደሚሆን ከወዲሁ እንጠቁማለን።

6."ማን ይምረጥ" የሚለው ቀጥተኛ ጥያቄ ምላሽ ያልተሰጠበት ዋንኛው ምክንያት ውሳኔ-ህዝቡ የሚካሄድባቸውን መልክዐ-ምድራዊ ክልሎችን መጠቆም ባለመቻሉ ነው። ከዋና ፀሐፊው ዘገባ ጋር ተያይዞ የቀረበ ክልሉን አመልካች ካርታ የለም። ህግሐኤ ለራሱ በራሱ ስልጣን ካርታ ነድፏል። ህግሐኤ በራሱ መስፈርት አዲስ ካርታ መንደፍ ለምን አስፈለገ? ምንስ ስልጣን አለው? የሚገርመው በመላው ዓለም እውቅናና ተቀባይነት ያለው የኢትዮጵያ (የኤርትራን ጨምሮ) ካርታ እያለ አዲስ የኤርትራ ካርታ ለምን አስፈለገ? ምንስ ይፈይዳል? ምናልባት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በጽሁፍ ሳይሆን በቃል ህግሐኤ ድሮ የነበረውን ካርታ በማስፋት ክልሉንም እንዲያሰፋ ስውር ስልጣን ሰጥቶት ይሆን? ይህ ምስጢራዊ ግንኙነት መጠቀስ የሚገባቸውን ጉዳዮች ካላጠቃለለ ሽፍጥ ለበስ የሆነ ውል ሊከሰት ስለሚችል ጥንቃቄ ይደረግበት እንላለን።

7.በተለያየ መልኩ ሲታይ ይህ ውሳኔ-ህዝብ ብዙ ጉድለቶችን ያዘለ ነው። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሚና በብዙ መልኩ የተገደበ ነው። አስፈላጊና መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች አልተሟሉም። ብቃትና ብዛት ያለው የሰው ኃይል ሊያሰማራ አይችልም። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የታዛቢዎች ቡድን ይህን በሚያክል ሰፊ የኤርትራ ክፍል ሶስት ስፍራዎች ላይ ብቻ እንዲወሰኑ ታዟል። እነኚህ ቦታዎች የሚገኙት በአስመራ፣ ከረንና በመንደፈራ አካባቢዎች ነው። ህግሐኤ አስፈፃሚ ኮሚሽኑን ማዋቀር ብቻ ሳይሆን በውሳኔ-ድምፁ ወቅት የቁጥጥር ዘዴዎችም እየቀየሰ ነው። ይህ የሚያመለክተው አብዛኛው የኤርትራና የአፋር ህዝብ ያለበት አካባቢ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቁጥጥርና እይታ ውጪ በመሆኑ በድምፅ መስጫው ወቅት

በታማኝ የህግአሌ ሠራዊት የማያምነውንና የማይቀበለውን ምረጥ ተብሎ እንደሚገደድ ለማንም ግልፅ ነው። ይህን አይነት ድርጊት ነው ድርጅቱ ህዝበ-ውሳኔው ነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተካሂዷል ብሎ ማህተሙን አስፍሮ ሊያፀድቀው የሚጣደፈው።

በመሆኑም ጉዳዩ የሀገር፣ የአንድነት፣ የወገንና የተተኪ ትውልድ ጥያቄ መሆኑን ክቡር ሊቀመንበሩ ተገንዝበው ከላይ በገለፅነው መሠረት ለውይይቱ መድረክ ያበቁን ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን።

ከታላቅ ክብሬታ ጋር

ፊርማ

ጉሹ ወልዴ
የቀድሞ የኢትዮጵያ ውጪ ጉዳይ
ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ መድኅን
ፓርቲ ሊቀመንበር

ግልባጭ

ለክቡር ሚስተር ሞሀመድ አ.አብዱላሰን
በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኩዌት አምባሳደር
ኒውዮርክ, ኤን. ዋይ. 10017

አባል ይሁኑ

የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማኅበር

የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ማኅበር

አ ባ ል ይ ሁ ኑ!

ከፍተኛ የእናቶችና የሕፃናት ሞት፣ ቁጥጥር ያልተደረገበት የሕዝብ ብዛት እድገት በጣም አነስተኛ የሆነ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ አቅም፣ በአብዛኛው ታዳጊ ሀገሮች የሚታዩ ክስተቶች ናቸው::

ችግሮችን ለማቃለል ከሚወሰዱት የልማት ተግባሮች የቤተሰብ እቅድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው እናምናለን:: ስለዚህም ይህንን ተግባር የሚያከናውነው የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማኅበር አባል በመሆን የበጎ ፈቃድ ድርሻዎን ሊያበረክቱ ይችላሉ::

የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማኅበር፣ የቤተሰብ እቅድ ኘሮግራም በኢትዮጵያ እንዲጀመርና እንዲስፋፋ በቀደምትነት የቆመና በበጎ ፈቃደኞች ተሳትፎ የሚመራ ድርጅት ሲሆን፣ የቤተሰብ እቅድ ኘሮግራም የእናቶች፣ የሕፃናትንና የቤተሰብን ጤንነት እንዲሻሻልና የተመጣጠነ የሕዝብ እድገት ከልማት ተግባር ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል::

የበለጠ ለመረዳት በሚከተለው አድራሻ ቢጽፉልን ወይንም በቴሌፎን ቢያነጋግሩን፣ ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ዝግጁ ነን::

የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማኅበር
ስልክ ቁጥር 15 21 96/51 41 11

የፖ.ሳ.ቁጥር 5716
አ ዲ ስ አ በ ባ



ማስነጠስ

ስለማስነጠስ ጉዳይ ጥቂት ላጫውትዎት። የጥንት ሰዎች ማስነጠስ ለሞት የመቃረብ ምልክት ነው ብለው ያምኑ ነበር። ስለዚህም አንድ ሰው ሲያስነጥስ "እግዜር ይርዳህ" ይሉታል። አደጋ ላይ ነው ብለው ስለሚያምኑ።

ሮማውያኖች ደግሞ የሚያስነጥስ ሰው ክፉ መንፈስን እንዳስወገደ አድርገው ስለሚያምኑ "መልካም እድል ላንተ" ይሉታል። መንፈሱን የማስ ወገድ ሙከራው እንዲሳካለት።

በ6ኛው ምዕተ ዓመት ገደማ ደግሞ ጣሊያን ውስጥ በተፈጠረው ችግር ታላቁ ጳጳስ ግሪጐሪ በማስነጠስ ጊዜ ፀሎት እንዲደረግ አዘዙ። (እኛም የሚያስነጥስ ሰውን "እግዜር ይማርህ" የምንለው ለዚህ ይሆን?)

ሳይንስ ምስጋና ይግባውና ማስነጠስ ከአፍና ከአፍንጫ አየር የማስወጣት ቅፅበታዊ ድርጊት ነው ይላል። ይህ ድርጊትም ከቁጥጥራችን ውጭ የሚከሰት ነው። ሲያብራራው ደግሞ በአፍንጫችን ውስጥ የሚገኘው ሚዩከስ ሜምብሬን የሚሉት ክፍል የነርቭ ጫፎች በሚረበሹበት ጊዜ ማስነጠስ ይፈጠራል። ከዚህም ሌላ አንቲክ ነርቭ የተባለው ክፍል ለኃይለኛ ብርሃን ሲጋለጥ፣ አንዳንድ የውጭ አካላት ባፍንጫችን ሲገቡና የአፍንጫችን ሚዩከስ ሜምብሬን ሲያብጥ፣ ጉንፋን ሲይዘን ወይም አለርጂ በሚያጋጥመን ጊዜ እናስነጥሳለን። ለምን? ማስነጠሱ አፍንጫችን ውስጥ ያለውን አላስፈላጊ ነገር ለማስወጣት ሰውነታችን አየር የሚልክበት ክስተት ነው።

ሞቃት ነገሮች ለምን ያቃጥሉናል?

ሞቃት (ትኩስ) ነገሮች ለምን እንደሚያቃጥልዎ ያውቃሉ? የጋለ ብረት በእጅዎ ነክተዋል እንበል። እንደሚያቃጥልዎ እርግጠኛ ነኝ። ለመሆኑ ምኑ ነው 'ተቃጠልኩ' ያሰኝዎት?

ነገሩ እንዲህ ነው። ሞቃት በሆነ ብረት ውስጥ ያሉ አቶሞች በከፍተኛ ፍጥነት ነው የሚርገበገቡት። ምናልባትም በሰኮንድ ውስጥ ሚሊዮን ጊዜ ያህል! ይህን ብረት በጣትዎ ቢነኩት ህመም የሚሰማዎት በብረቱ ውስጥ ያሉት በፍጥነት የሚንቀሳቀሱት ፓርቲክሎች (Particles) በቆዳዎ ውስጥ ያሉትን ሞለኪሎች በድንገተኛና ግብታዊ በሆነ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገቡ ስለሚያደርጉ ይህ ድንገተኛ እንቅስቃሴ ህመም ይሆንብዎታል።

እንዲህ ያለ ህመም እንዲሰማዎት ያደረጉት ሞለኪሎች እንቅስቃሴ ምን ያህል ቢሆን ነው ብለው ይገረሙ ይሆናል። ትንሽ ሃሳብ ልስጥዎት። ለምሳሌ ምንም ያህል ሞቃት ነው በማይባለው በረዶ በሚቀልጥበት ቴምፕሬቸር የሃይድሮጂን ሞለኪሎች በሰኮንድ ጊዜ ውስጥ 1,700 ሜትር (1,700m/s) ባለው ፍጥነት ይንቀሳቀሳል። ሙቀቱ ብረትን የማጋል ያህል ቢጨምርስ? ስሌቱን ለእርስዎ እተዋለሁ።

የአዕዋፋት አስገራሚ ሚስጢር

የተፈጥሮ አንዱ አስገራሚና አስደናቂ ሚስጢር የአንዳንድ ፍጥረታት ከረጅም ርቀት ጉዞ በኋላ ቤታቸውንና መንደራቸውን ለማግኘት መቻላቸው ነው። ይህን መሰሉ ችሎታ የወፎች ብቻ ሳይሆን ንቦችም ከረጅም ርቀት ጉዞአቸው በኋላ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ተመልሰው መምጣት ይችላሉ።

ታዲያ ወፎችን ቤታቸውን ለቀው ረጅም ርቀት ከተጓዙ በኋላ ቀድሞ ወደ ነበሩበት ቦታ የሚመራቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ በርካታ ምርምሮች ታካሂደዋል። በአንድ ምርምርም ስባት ስዋሎ (Swallow)የተሰኙ የአዕዋፍ ዝርያዎች ከጐጆአቸው 400 ማይልስ ርቀት ተወስደው ሲለቀቁ እምስቱ ወደ ቀድሞ ስፍራቸው ተመልሰዋል። በሌላ ጥናት ደግሞ የባሕር ወፍን ዌልሽ ኮስት ከሚገኘው ወደብ አካባቢ ካለው ጐጆው በአይሮፕላን በቀጥታ የበረራ ርቀት 930 ማይልስ ወደ ቬኑስ ተወስዶ ሲለቀቅ እሱም ወደ ጐጆም ተመልሷል።

የሚሰደዱ አዕዋፋት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። ከኢንግላንድ ወደ ደቡብ አፍሪካ በየአመቱ የሚሰደዱ ስዋሎዎች ዓመት ወደ ኢንግላድ መመለስ ብቻ ሳይሆን አብዛኛዎቹ ወደ ቀድሞው ጐጆዋቸው ነው የሚገቡት። እንግዲህ የተጓዙበት ርቀት ምን ያህል መሰለዎት? 6000 ማይልስ!

በነገራችን ላይ አንዳንድ የቢራቢሮ አይነቶችም የሚሰደዱ መሆናቸውን ያውቃሉ? እነሱም ሲመለሱ መንገዳቸውን ያውቁታል። በትሮፒካል አካባቢዎች በርካታ ቢራቢሮዎች እንደ አቅጣጫ ይዘው ሲበሩ ማየት ይቻላል። በሺህ የሚቆጠሩ ማይልሶችን ተጉዘው ሊሄዱና በሌላ ወቅት ደግሞ ሊመለሱ ይችላሉ።

ሚስጢር የሆነው ጉዳይ እነዚህ ፍጥረታት እንዴት አቅጣጫቸውንና ቤታቸውን ለመለየት እንደ ሚችሉ ለማወቅ በርካታ ሙከራዎችና ጥናቶች ቢካሄዱም ለማወቅ አለመቻሉ ነው። መሬት ላይ ያሉ ምልክቶችን እየተመሩ ነው እንዳይባል አዕዋፋቱቹ በውቂያኖስ ላይ ረጅም ርቀት ይበራሉ። በደመ ነፍስ ነው እንዳይባል ደካማ መላምት ይሆናል። ፍጥረታቱ የሚጠቀሙበት መሪ አካል ለሰው ልጅ ሳይታወቅ የቀረ ሚስጢር ሆኗል።

ግራኞች

ሊዎናርዶ ዳ ቪንቺንና ሚኬኤል አንጀሎ ግራኞች እንደሆኑ ያውቃሉ? ግራኝ መሆን ምንም ችግር የለውም። ሆኖም ወላጆች ልጆቻቸው ግራኝ ሲሆኑባቸው ይጨነቃሉ። ከአለማችን ውስጥ ደግሞ ፬፻ የሚሆኑት ግራኞች በመሆናቸው ይህቺ አለም የቀኞች መሆኗ ቢስተዋልም ግራኝ መሆን የሚያስከትለው ችግር እምብዛም አልተስተዋለም።

አሻራ

የጣት አሻራ ወንጀለኞችን ለመያዝ የሚያስችል አማራጭ መሆኑ ለእርስዎ አዲስ ነገር ባይሆንም ጥበቡ በሳይንስ የተረጋገጠው በቅርብ ጊዜ ውስጥ መሆኑን ልንገርዎት። አሻራ ያን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው ያረጋገጠው የመጀመሪያው ሰው ዶክተር ሄንሪ ፋውልድስ የተሰኘ እንግሊዛዊ ሲሆን ወቅቱም በ1880 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ነበር። በ1892 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ፍራንሲስ ጋልቶን የተባለ ታዋቂ እንግሊዛዊ ሳይንቲስት ሁለት አሻራዎች (የሁለት ሰዎች) ተመሳሳይ አለመሆናቸውን በሳይንሳዊ ምርመራ አረጋገጠ። የአሻራ ሪኮርዶችንም ሰብስቦ ለማዘጋጀት የመጀመሪያው ሰው ነበር።

የብሪቲሽ መንግስትም የሳይንቲስቱን ሃሣብ በመቀበል አሻራን በመጠቀም ወንጀልኞችን ለመለየት የሚያስችለው ዘዴ ጥናት እንዲደረግበት አዘዘ። የምርምር ኮሚሽኑ አንዱ አባል ኤድዋርድ ሄንሪም በኋላ የስኮትላንድ ያርድ የበላይ ኃላፊ የሆኑ ናቸው። (ስኮትላንድያርድ የሚባለው የብሪታንያ የሜትሮፖሊታን ፖሊስ ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ነው)

ሄንሪም አሻራን የመደልደልና በአይነት የመመደብን ዘዴ ቀየሱ። ይህ ዘዴ ሁለት አይነት አሻራዎችን ለመለየት የሚያስችል ቀላል ዘዴ ነው። በሄንሪ ዘዴ መሠረትም የጣቶችን ሁናቴ በሰባት ክፍሎች በመከፈል ያስቀመጡት ሲሆን በዚህም ስልት አስሩን ጣቶች በየመደባቸው ለይቶ ማስቀመጥ ይቻላል ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ኤፍ. ቢ.አይ. የተባለው የአሜሪካ የወንጀል ምርመራና ቁጥጥር ድርጅት (ፌደራል ቢሮ ኦቭ ኢንቨስቲጌሽን) በ1908 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ተቋቁሞ የድርጅቱ የመታወቂያ ዲቪዥን (ክፍል) በ1924 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ሲመሰረት በ810,188 የአሻራ ስብስቦች ሥራውን ጀምሮ በአሁኑ ጊዜ ከመቶ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎችን የእጅ አሻራ ካርድ ሰብስቦ መያዙን ያውቃሉ?

ስለዚህ የመታወቂያ ክፍል (ዲቪዥን) ትንሽ ላጫውትዎ። ይህ ክፍል የወንጀለኛ ዳታዎችንና ለአሻራዎች ማዕከላዊ የመረጃ ክፍል ሲሆን አንድ ግለሰብ በሚታሰርበት ጊዜ ከታሰረበት ክፍል አሻራው ወደዚህ ዲቪዥን ይላክና ይህ ዲቪዥን በአምስት ደቂቃ ውስጥ እስረኛው የወንጀል ሪኮርድ ያለበት መሆን አለመሆኑን ይለያል። የዚህ ግልባጭም (ኮፒው) የአሻራው ካርድ ዋሽንግተን ከደረሰ (ኤፍ.ቢ.አይ.መታወቂያ ቢሮ ያለበት ከተማ) በ36 ሰዓታት ውስጥ ጉዳዮን ለጠየቀው ክፍል ይላክለታል።

ትንባሆ

የዛሬ ዘመን ትንባሆ ጠጭ ለምን እንደ ሚያጨስ ሲጠይቁት አጥጋቢ ምክንያት የሚሰጥ አይመስለኝም። ጉንፋን ያበስላል ሃሣብ ይከፍላል ወዘተ ሊሆኑ እነዚህም ከመንገድ ዳር የተጠለፉ ምክንያቶች ደጭ አንጀት ጠብ አይሉም። በዚህ በዚህስ እኒያው የጥንቶቹ ሳይሻሉም አይቀሩ። እንዴት ቢሉ እንዲህ ነው ነገሩ። ነገርን ከስሩ እንዲሉ።

የደቡብና የሰሜን አሜሪካ ህንዶች ትንባሆን ለማምረት ቀደምት ናቸው። የሰሜን አሜሪካዎቹ ህንዶች ትንባሆን በአንዳንድ በዓሎቻቸው ላይ በማጨስ የሚዝናኑ ቢሆንም አብዛኞዎቹ ትንባሆ የመድሐኒትነት ፀባይ አለው ብለው ያምኑ ነበር። በእርግጥም ትንባሆ ወደ አውሮፓ ሊዛመት የቻለው በመድሐኒትነት ሰበብ ነበር።

አውሮፓ ውስጥ ከታወቀ በኋላ ተክሉን ማምረት በሌሎቹም የተቀሩት ሃገራት ተሰራጨ። በዚህም መሠረት ፈረንሳይ በ1556 ዓ.ም.፤ ፖርቱጋል በ1558 ስፔይን በ1559 ኢንግላንድ በ1565 ኩባ በ1580 ቨርጂኒያ በ1612 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ትንባሆን ያመርቱ ጀመር።

ይህም ሆኖ ትንባሆ በመጀመሪያ ሲታወቅ ሰው ሁሉ የማጨስን ተግባር አልፈቀደውም ነበር። እንዲያውም ባንድ ወቅት ቱርኮች የሚያጨስን ሰው በሞት ሲቀጡ የሩሲያው ንጉስም ትንባሆ የሚጠጡትን ሁሉ አፍንጫቸውን ተቆርጠውና ተገርፈው ወደ ሳይቤሪያ እንዲጋዙ አዝዘው ነበር።

ዛሬ ግን ትንባሆ (ሲጋራ፤ ሲጋራ ፒፖ) በየትኛውም የአለም ክፍል ተሰራጭቶ በአደባባይ መጨሱ የአደባባይ ሚስጢር ቢሆንም ሣይንስ በጥናቱ ጉጂነቱን እያረጋገጠ በሄደ ቁጥር የአጫሾች ቁጥርም እየጨመረ መጥቷል። በአሁን ወቅት አሜ

ሪካ የአለምን የትንባሆ አምራችነት ወድድር በሻምፒዮንነት እየመራች ትገኛለች።

"እግዚአብሔር እንድናጨስ አልፈቀደልንም። ቢፈቅድልን ኖሮ ጆሮ ግንዳችን ላይ ጭስ ማውጫ ይሰራልን ነበር። " የሚለውን አባባል የተናገረው ሰው ቁም ነገር መናገሩ እውነት ሲሆን አጫሾች ልብ የሚገዙት መቼ ይሆን?

-ትርጉም:-እየለ እሸቱ

ምንጭ:-
"TELL ME WHY"
by Arkady Leokum

ይህን ያውቁ ኖሯል?

(ኪያሬድ በላይነህ)

-ምንጭ:-ሪደርስ ዳይጀስት

መንግስት ግልበጣ

በ1825 እ.ኤ.አ. ነፃ ግዛት ከሆነች በት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1984 ድረስ 191 ጊዜ ኩዴታ የተከናወነባት ሀገር ቦሊቪያ ናት። የመጨረሻው ኩዴታ የተደረገው በ1984 እ.ኤ.አ. ሲሆን ይኸውም 60 የታጠቁ ሰዎች የ70 ዓመቱን ፕሬዚዳንት (ሔርናን ሳይልስ ዙዋዞ) ከመኖሪያ ቤታቸው አፍነው የወሰዱት ነው። በዚህም የኩዴታ ብዛት ቦሊቪያ የዓለም ክብረ-ወሰን መዝገብ ላይ አርፋለች።

እጅግ አሰልቺው የመሪ ንግግር

በዓለም ላይ እጅግ አሰልቺና አታካች የመሪ ንግግር የተደረገው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስብሰባ ላይ ሲሆን ተናጋሪውም የኩባው ፕሬዚዳንት ፊደል ካስትሮ ሩዝ ናቸው። እ.ኤ.አ. መስከረም 26,1960 በተደረገው ስብሰባ ላይ 4 ሰዓት ከ29 ደቂቃ የፈጀ ንግግር አድርገው ነበር።

ጅምላ እስር

በርካታ የጅምላ እስር ዘገባዎች ቢመዘገቡም እስከ ዛሬ ወደር ያልተገኘለት በደቡብ ኮርያ የተደረገው ሲሆን ይኸውም በ1988 እ.ኤ.አ. የሲኦል ኦሎምፒክ ዋዜማ ላይ የወጡትን 15,617 ሰላማዊ ሰልፈኞች በሙሉ ፖሊሶች ከበው ወህኒ ያጉሩዋቸው መሆኑ ታውቋል።

የቃላት ብዛት

በዓለም ከሚነገሩ ቋንቋዎች ውስጥ እንግሊዝኛ በርካታ ቃላቶች እንዳሉት ይታመናል። በዚሁ መሠረት በግምት 490,000 ቃላቶችና 300,000 ሙያ ነክ ቃላቶች (Technical Words) በውስጡ እንዳካታታ ይገመታል። ሆኖም ማንኛውም የቋንቋው ተጠቃሚ ግለሰብ 60,000 የሚደርሱ ቃላት መጠቀሙ ያጠራጥራል።

ረጅም ጊዜ የወሰደው የረሀብ አድማ

በታሪክ መዝገብ ከተመዘገቡት የረሀብ አድማዎች ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተካሄደው በእንግሊዝ ሀገር ዌክፊልድ በሚባል እስር ቤት ውስጥ ዴኒስ ጋለር በተባለው እስረኛ ሲሆን ለ385 ቀናት አድማውን እንዳደረገ ተመዝግቧል። መንስኤውም ባልፈፀመው የሀሰት የሴት መድፈር ወንጀል ክስ ሲሆን በመጨረሻም በግድ በአፉ ቱቦ በማስገባት ሊመግቡት እንደቻሉ ተመዘግቧል።

ረጅሙ ፀጉር

ዲያና ዊት ትባላለች። አሜሪካን ሀገር በማሳቹሴት ክ/ሀገር ነዋሪ የሆነችው ዲያና እ.ኤ.አ. በ1975 ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፀጉሯን ተቆርጣ ነበር። በ1989 ማለት ከ18 ዓመት በኋላ ፀጉሯ ሲለካ 3 ሜትር ከ8 ሳ.ሜ ሲሆን ለመታጠብ 4 ሰዓት እንደሚፈጅባት ታውቋል።

ትልቁ የአውሮፕላን ጠለፋ ካሣ

ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብና ስድስት ከባድ ወንጀለኞችን አሳልፎ ለአውሮፕላን ጠላፊዎች የከፈለው የጃፓን መንግስት ነው። ይኸውም እ.ኤ.አ. ጥቅምት 2,1977 የጃፓን አየር መንገድ (JAL) መለያ ቁጥሩ ዲሲ-8 በባንግላዴሽ ዳካ አውሮፕላን ማረፊያ በታገተበት ወቅት ነበር። በዚህም አግባብ የሌለው የወንጀለኞች ካሣ ክፍያ የጃፓን መንግስት የክብረ-ወሰን መዝገብ ላይ ተመዝግቧል።

ረጅሙ ጠም (ፂም)

በዓለም ላይ ባለ ረጅሙ ፂም ተብሎ የሚታወቀው የኖርዋይ ተወላጅ ሀንስ ኤን ላንግሴዝ ሲሆን በሀኪምና ባለሙያዎች እንዳይበላሽ ጥንቃቄ ተደርጐለት በህዝብ እየተጐበኘ ያለው ፂሙ 5 ሜትር ከ33 ሳ.ሜ ርዝመት እንዳለው ተነግሯል።

ውድ ዋጋ ያወጣ ጥርስ

በ1816 እ.ኤ.አ. በእንግሊዝ ሀገር የይሳቅ ኒውተን ጥርስ 1100 ዶላር እንደተሸጠ ሲመዘገብ የጥርሱ ገዥ አንድ የእንግሊዝ መኳንንት ሲሆኑ ሁሌ ከጣታቸው በማትለየው ቀለበታቸው ላይ በማስገጠም ለብዙ ጊዜ እንዳኖሯት መረጃዎች ይጠቁ..ሉ።

ሥነ ጥበብ

የኔ ሕይወት የሳት እራት

(ሰለሞን እምባቸው አልጣህ)

(ከልደታ)

ጭር ባለው ሌሊት ብቻዬን ነኝ። እሜዋችም አልሻ። "አይ ዞሀ" ባይም አልፈልግ። ዘመናት የማይሸፉት ትግል አለኝ። የሀ ሊና ትንቅንቅ። ከእኔነቴ ጋር ዘወትር እጣላለሁ። እሸናፊው አይ ታወቅም። ውጤትና ድል አልባ ጦርነት ነበር። ዛሬ ወንድና ሴቱ ይለያል፣ ብርቱው ይበረታል። የቀጠሮ ሰዓታችን ደርሷል።

በፈጣሪ ልዩ ስራ፣ ልዩ ምስጢር ገብቼ ህይወትን በማወቅ ፍልስፍና ስባዝን ዕድሜን ፈጀሁት መስል ትዕግስት አጣሁ። ቅብጥ ብጥ አደረገኝ። ሌላ ስም የላት ሆነና፣ ሌላ መጠሪያ አጣሁላትና እኔም እንደ ሰው"ህይወት" አል ኳት ህይወት መሳይ ህይወቴን። ይጨንቀኛል። የማላውቀው ሃሣብ ህለናዬን ወጥሮቷል። የህይወት ጥማት። ደግነቱ በስተማብቂያው፣ በስተመጨረሻው ሆነ እንጂ ያለፈ ኑሮዬ እንዳሁኑ የተስፋ ድባብ የራቀው ቢሆንማ ኖሮ ምን ይውጥኝ ነበር?።

ለአመታት በየለምለሙ አረ ንጓዴ የሳር ምንጣፍ የልምላሜ ሜዳ፣ በየአበባው፣ በየፅጌረዳው የመዐዛ ጠረን ሽታ በሚያውድበትና "አለች ትኖራለች" በተባለችበት ስፍራ ሁሉ ያለእንዳች መታከት ስፈልጋት ከረምኩ። ህይወቴን። የኔን ህይወት። ጉልበቴን፣ ሐይ ሌን፣ ህሊናዬን በአንድ ደምሬ በምድረ ገነት በደስታው ቀዬ አሰ ስኳት። የለችም። ዛሬ ሲሰለች ኝና ተስፋ መቁረጥ በውስጤ ሲሰለ ጥን "እመጣለሁ በመቅረዝ ነበል ባል ጋልቤ እድርሳለሁ" ብላ ላከ ችብኝ። ትምጣ። ወገቤን ታጥቄ እጠብቃታለሁ። ሌላው ቀርቶ እውነ ተኛ ሰሟን እንኳን ባውቅ ብዬ።

አይዋጠኝም። የህይወት ቢራቢሮነት ይተናነቀኛል። ድር ሳነ-ገድሏ፣ ምስለ ምስሏ አይገባ ኝም። ተስፋ ቢስ መሆን ይሆ ናል። እንጃ። ድርጊቷን ገላጭ ስም አጣሁና ሲሉ እየሰማሁ የህይ ወት ጥላ ህይወቴን "ህይወት" እያልኩ ሳቆላምጣትና ሳሞካሻት ኖሬአለሁ። ግና ዛሬ እንዳዘዘ ችኝ የሳት ዳቦ ቆርሼ፣ የመቅረዝ ነበልባል አጋግሜ ስም ላወጣላት፣ መንፈስን በአካል ለመገናኘት እየ ጠበቅሁ ነው። አሁን ይቀናኝ እንጂ።

የመቅረዙ ነበልባል እሳ ታማ ቀስት ቀጥ ብሎ ወደ ሰማይ ተንጣጥሯል። የምስራው የማደር ገው ባጣ ትኩር ብዬ ባስተውሎ ወርቃማ ቅጠሉን መመልከት ጀም ርኩ። ፈተና መሰለኝ የመኖር ፈተና። ስቃይ መሰለኝ የህይወት ህቅታ። የቀጠሮአችን ሰዓት እየ ተቃረበ ነው። ሌቱ ተጋምሷል። እንደማትቀር ባውቅም እቅበጠበ ጠኝ። እንቀጠቀጠኝ። እንዳበ ሽቀችኝ ላበሽቃት፣ እንዳነደደችኝ ላነዳት ብዙ አስቤአለሁ። ብዙ ብዙ። ደግሞ እቧን ብሎ ውብ፣ ደማቅ፣ ሸጋ ቢራቢሮ ድንቂም፣ እቧነቷን አልሻም። ብቻ ለግብሯ ገላጭ የሆነ መጠሪያዋን ብቻ። የኔን ህይወት። በመለኮት ሐይል የተከበበችዋን፣ በመንፈስ ስልጣን የታነፀችዋን።

የዕድሜ ይፍታህ ጉዞ "እጅ እጅ" ብሎኛል። ጣዕሙ ሰንፍጦኛል። እስከመቼስ ይሆን የኔም ህይወት "ህይወት ቢራቢሮ" ተብለሽ በወል ስም በሽጉቱ ፍጡ ራን ስም ስትጥሪ የምትኖሪው? እስከመቼስ ነው በመሰሎችሽ ካባ ተሸምለሽ በሽፍንፍን የምትዘል ቂው? እናስ የኔ ህይወት ማን ነሽ? መገኛና መኖሪያሽስ ወዴትና እንዴት ነው? እውን ህይወቴ ህይወት ነሽ?። ቢራቢሮ።

በወራት ከፈን ተከፍና፣ በቀናት ውታፍ ተወትፋና በዓመታት ልግም ተሸብባ በሁለንተና፣ በሁለ መና ትኖራለች። የትም። ዛዲያ ብሽት ንድድ ታደርገኛለች። ለዘ መናት ሲያስጨንቀኝ የከረመው የቀ ቢፀ-ተስፋ ፍልስፍና ዛሬ ይጠና ቀቃል።

ህይወት ማለት ምንድን ናት? ትርጓሜዋስ እንደምን ነው?። አሁን አሁን ሳስበው ጅልነቴና ሞኝነቴ ይገርመኛል። የሰው "ህይወት ቢራቢሮ" ልብ ትመስለኝ ነበር። ግና ስንቱ ልበ-ቢስ ልቡንና ቀልቡን ጥሎ ባዶ ቀፎውን ሲወዛወዝ"ህይወት ልብ ናት" የሚለውን ጥሬጣሬዬን ፉርሽ አደረገዋለሁ። "አይ ህይ ወት አናት"ናት እላለሁ። ደግሞ ሌላ ጊዜ ራስ አልባ የሆነ ሃሣብ-ቢስ ነሁላላ ሲያጋጥመኝ አሁንም ህይወት ጭንቅላት የመሆ ኗን እሳቤ እጥለዋለሁ። እንዲህ እንዲህ እያሰብኩ ስም የለሽ የኔ ይቱን ጉድ በመቅረዙ ነበልባል እጠብቃታለሁ። እጅ፣ እግር፣ አይን፣.....ካልሆነች ህይወት ማለት ምንድን ነች?።

ከፈጣሪ ጉልበትና ሐይል የተሰጣት የነገስታት ንጉስ፣ የጌ ቶች ጌታ፣ የሀያላን ሐያል ጠረኛ ተዋጊ "ሺ በከንቾ ሺ ባክናቾ" በሰማይ ጋላቢ ትሆን? ይሄ ከሆነ ቤቱ በጣም ጠባብ ነው። እለበ ለዚያ እቅመ ደካማ ፊቷ የተሸበ ሸበ ባልቴት። ሲነኳት ስምሽታ የምትሰበር። ሲጨብጧት የምትልም ደቃቃ ትሆን?። እንጃ። ዛሬ ሁሉ ይለያል። የመቅረዙ ቀስት ምስክሬ ነው። ብምራት አይማ ረኝ፣ ብተዋት አይተወኝ። ባሳድ ራት እያሳድረኝ። ህይወቴን።

የሰው "የህይወት ቢራ ቢሮ" በሌት ከከዋክብት ፍንጥቅጥ ቃት ተመሳጥራ ከባዘቶው ፀዐዳ ሆጨጭታ ጋር አብራ ጨረቃን እያጀ በች በብርሃን ሸማ በምትምነሽ ነሽበት ባሁን ሰዓት፣ በፀጥታና በዝምታ ኗሪዎቿን የደስታና የፍ ቅር በርኖስ ከላያቸው ደርባ ባማረ እልፍኝ በሞቀ አልጋ አስ ተኝታ እሷም ተራዋን ልትፈነጥዝ ከከዋክብትና ከጨረቃ ስርግ ለመታ

ደም በአየር ተንሳፋለች። የኔዋ
ገልቱ ግን ለቧንቷ ሀሊናዬን
አስገዝቼ በኪኑት ጥበቤ በብዕሬ
ስከሽናት በኖርኩ አልያዘኝ አልጨ
በጠኝ ብላ ስትሟወትብኝ ከረመች።
ዛሬ ደግሞ ተስፋዬ ሲሊቃለት
በጠፋ ጨረቃ፣ በእኩል ሌሊት
መቅረዝ አብሪቹ እጠብቃት ዘንድ
ላከችብኝ።

ከደማሟ ንጋት አብራ
ነግታ ወርቀዘቦ ወርቅ ንክር
እግሯን ከምስራቅ ተራሮች ጉያ
አንፈራጣ ትዘረጋና የሰው ህይወት
አለሳልሳ "ተነሱ" ትላቸዋለች።
ባለ ቢራቢሮዎቹም በደስታ ስክ
ረው"ከአመት አመት ደምረን፣
አመት አመት ድገሚና ድገሚና" እ
ያሉ በሆታና በፀሎት-ምስጋና ማል
ደው ይነቃሉ። የእድማሳቱን የደ
መና ግርዶሽ ትቀድና ተምዘግዝጋ
ከሲጋቸው ትጨመራለች። የሰው"ህ
ይወት ቢራቢሮ"።

በአበቦች ወራት ከአበቦች
ጋር ባረንጓዴ መልከ-ልምላሜ
ተውባ፣ በፀደይ ወራት አቆጥቁጣ
በፀዳል ውብቷ ስታስጌጣቸው "ህይ
ወት ቢራቢሮ" ይሏታል። ንድድ
ብሽቅ ይለኛል። ቅናት ግን ተፈ
ጥሮዬ አይደለም። ቀን በፀሐይ
ብርሃን ተሞሽራ፣ ከዝናቡ ዘንባ፣
ከነፋሱ ነፍሳ፣ ከመብረቁ በርቃ፣
ከንጉቴው፣ ተንጉጉታ ሲያልፍላት
በሰማይ ቀስተ ደመና፣ የኖህን
የቃል ኪዳን መቀነት ታጥቃ፣ የም
ስራች ነጋሪት እየደለቀች ትዘፍና
ለች። ያን ጊዜ እሷን "የህይ
ወት ቢራቢሮ" ይሏታል። አለመ
ኖች።

ትሰሚያለሽ? የኔዋ የህይ
ወት አምሳል ህይወቴ። የሰው
ነፍስ ቢራቢሮ እኮ ጠፊም ከታሚም
ብትሆን ለአፍታ ለሽራፊ ደቂቃ
እንኳን ቢሆን በዓለም ዙሪያ
በፀጋ ትሽከረከራለች። ወዘናዋና
ፀዳሏ ለሰከንድም ቢሆን ከፊቷ
ሲፈስ ይታያል። በአደይ አከሊል
እንደ አዲስ ሙሽራ ተከፍክፋ
"እንትፍትፍ" ተብላ፣ ተስማ፣
ተመርቃ ባይሆን.....። አንቺ
የኔዋ ግን እንጃልሽ።

ሁሌ ለቅሶ፣ ሁሌ ዋይታ፣
ሰርክ ኡኡታና ከላላይሶ አይሰለ
ችሽም። ወይ ዕምባሽ ጉርፍ
ሰርቶ ጠርጎ ቢወስድሽ ግልግል
ነበር። ዳፉ ከየት ተገኘተሽ።
ዕድሜዬን ሙሉ ከላዬ ተላጥቀሽ
መከራዬን ታበዪኛለሽ። ቆይ ግድ
የለም ዛሬ ብቻ ቶሎ ነይ እንጂ
እስራልሻለሁ። ለርሙ አንድ ቀን
ቢራቢሮነትሽን ሳላይ፣ አንቺም
እንደሰው "ህይወት ቢራቢሮ"
አንድ ቀን ለመጥራት መዝጊያዬን
ትቀበቅቢ ይሆናል። አዎን አንቺ
ምን ይሳንሻል። "ተኖረና ተ
ሞተ" አሉ አለቃ።

ፍጠኝ። ዛሬ በጨለማ
ልገናኝሽ ነውና ቸኩይ። ተጣ
ደፊ። ደግሞ አንቺን ብሎ ህይ
ወት። ህይወት መሳይ ህይወት።
ባዶ፣ ወና፣ ጭላጭ፣ ንቃሪ።
አዎና ሰደብኩሽ ምን ትሆኝ?።

በድንገት የመቅረዙ ነበል
ባል ተርገበገበ። የሳት ቀስቲ
ተንቀጠቀጠ። እራቱን ሊበላ ችቦ
ው የመሰዊያ ስለቱን ሳለ፣ ሰይ
ፉን አፏጨ። መጣች መሰለኝ።
እሳት እንኳን ፈርቷት ሲብረ
ከረከ። ገረመኝ።

እነሆ ባየሁዋት ጊዜ ቅፅ
በታዊ ፍርሀት ዋጠኝ። የኔዋን
ህይወት እየሁዋት። እንግዳይቱን
የኔን ህይወት ድምፄን አጥፍቼ
ባስተውሎ በስተገርሞ ተመለከ
ትኳት። ይህቺ ናት ህይወቴ?
ይህቺ ምናምንቴ ናት ለዓመታት
ያስቃየችኝ?። ነደደኝ። በቀል
አቃጠለኝ።

ቢራቢሮ መሳይ፣ የምትበር
ነፍሳት። በመብረሯ ብቻ "ቢራ
ቢሮ" የተሰኘች ቢራቢሮ ሐምሳል
ግን ጭራሽ ውበት አልባ። አይን
የማትገባ፣ መልከ-ጥፉ ማስጠያ፣
መጣጣ፣ የደም ገንቦዋ የተሰበረ።
እንደ ፀደይ የፀደይ ቀለም
የሌላት ብቻ በላዩዋ ላይ ማቅ
ነስንሳ ትቢያ ነፍታ ከለብላቢው
የመቅረዝ ነበልባል "ልዶል" ብላ
የምትሽከረከር፣ እልሽኛ ፍጡር
አየሁ።

የሳቱን ቋያ እየዞረች
ዳንኪራ መርገጥ ጀመረች። ቃናው
ንና ቅላጼውን በሳተ ድምፅ ዘፈ
ነች።

"እኔ ስሜ የሳት እራት
ሰርክ ምሴ ሰደድ እሳት
መልከ-ጥፉ ውበት አልባ
የሳት ደመራ እንጂ አል
ሻም አበባ"

እያለች ደስ በማያሰኝ ጉርናና
ዜማ አዜመች። የሰው "ህይወት
ቢራቢሮ" አበባውን ስትዞር የኔዋ
አስቀያሚ ግን እሳትና አመድ እን
ደጋኔል በውድቅት መፈለጓ ቢያናደ
ደኝም እውነተኛ ስሟን በማወቄ
ደስ አለኝ።

በጁ ገፍትሬ ከሳቱ ልጨ
ምራት አሰብኩና ተውኩት። የመቅ
ረዙን ነበልባል መሐል ለመሐል
ሰንጥቃው አለፈች። ዘገነነኝ።
ሰቀጠጠኝ።

"አባክሽን የኔ ህይወት
ስላንቺና ላንቺ ተፈጥሬ አንቺም
ለኔ ተፈጥረሽ ለአንድ እኔሽ ለአ
ፍታ እንደምን ቢራቢሮ መሆን
አቃተሽ? ስለምን እኔን በሳት
ሰነድ የኖርኩትን ያ መከራዬ አን
ሶኝ ደግሞ በሳት ልትጠብሺኝ
አሰብሽ?" እያልኩ እልህና ቁጭት
ባመነጨው ዕምባ ለመንኳት። እሷ
እቴ ግድም አልሰጣት። ፍጥነቷን
ጨምራ መሽከርከሯን ቀጠለች።
በሽኩኝ፣ ነደደኝ። ለጥሪ ጨክና
በሬን ለመምታት መምጣቷ ገባኝ።
"ዳፋ አንቺ ምን ቀልብ አለሽና።
ደግሞ አንቺን ብሎ ህይወት።
'ህይወት ቢራቢሮ'። የሳት እራ
ት። ዕረፍትና እፎይታ ላማራት
ህይወትሽ ወዮላት! ወዮላት!"
አልኳት በንዴት በግኜ።

የመሽከርከሪያ ምህዋሯን
እያጠበበች እያጠበበች ሄደችና
ከሳቱ ቋያ ተደረገመችበት። ተን
ጫረረች። ጨሰች፣ ተቃጠለች።
እፎይታ።

ግን በስቃይ እየተቃጠለች
ዘፈኗን አላቋረጠችም።

"እኔ ስሜ የሳት እራት....."
ትል ነበር።

ሀሁ ወይም ፐፑ

(ከተስፋሁን ፀጋዬ)

"ቴአትሩ ካለቀ በኋላ ግን እንደጥሩ የኪነ-ጥበብ ሥራ ውስጥህ የሚቀር ነገር የለም። ግራ የሚጋባ ቴአትር ነው።.....ቴአትሩ ሲያልቅ ግን ስለምንድን ነበር? ብለህ ራስህን ብትጠይቅ ምንም የተከናወነ ነገር እንደሌለ ትረዳለህ። ብዙ ስድብ፤ ጥቅጥቅ አለበት፣ በቃ!" ይህን ቃል-በቃል የተናገሩት የብሔራዊ ቴአትር ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ማንያዘዋል እንደሻው ናቸው። ለእፎይታ መጽሔት አንደኛ አመት ቁጥር 7 ለተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ "ሀሁ ወይም ፐፑ" በሚል ርዕሥ በባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ተደርሶ በእሁኑ ሰዓት በብሔራዊ ቴአትር ቤት በመታየት ላይ ስላለው ቴአትር የተሰማቸውን ሲናገሩ።

እንኳንስ የቴአትሩ ይዘትና ብቃት፣ እንኳንስ የተዋንያን ገፀ-ባሕሪውን በአግባቡ የመወከል ስምረት፣ እንኳንስ አልባስ፣ ቅብና ስሙር የመድረክ ዝግጅት ሊኖራቸው እጅግ በተሰላቸና በተንዛዛ ማሕበራዊ ጭብጥ ዙሪያ፤ ቀሊል ቴክኒክና አቀራረብ ይዘው መድረኩን በባዶ ጩኸትና ትርምስምስ ሞልተው ሙያውንና ህዝቡን መነገጃ ያደረጉትን "የመድረክ ቡቲኮች" ነቅሼ፤ እነዚህን ዛሬ-ዛሬ በየቴአትር ቤቱ የፈሉ "ቴአትር ያልሆኑ ቴአትሮች" ጠቁሜ፣ ቴክኒካዊ ይዘታቸውንና ጥበባዊ ፋይዳቸውን እያነፀርኩና እያነጠርኩ መሞገት የተነሳሁበት ርዕሰ-ጉዳይ አይደለም።

መንገዴ የአቶ ማንያዘዋል እንደሻውን አስተያየት (እፎይታ መስከረም 1985) ተንተርሼ በ"ሀሁ ወይም ፐፑ" ቴአትር ላይ የተሰማኝን አስተያየት ለመግለፅ ነውና የበኩሌን አንድ ልበል።

እንደማንኛውም የጥበቡ ዘርፎች ቴአትርም በተለያዩ ጉዳዮች አነሳሽነት፣ ለተለያዩ አላማዎች በተለያዩ ዣንሮች ሊፃፍ እንደሚችል እናውቃለን። በመሆኑም በመሠረተ-ሃሣቡ ደረጃ 'ቴአትር ሁሉ ከሰዎች ሕሊናና ስሜት ውስጥ ተሰንቅሮ የሚቀር ስሜት ማስቀረት አለበት' ባንልም "ሀሁ ወይም ፐፑ" በሚለው ቴአትር ላይ የተሰጠውን የአቶ ማንያዘዋል እንደሻውን ብይን ስንገመግም ምን ተልዕኮና አቅጣጫ እንዳለው መተንተን አያሻም። ማንኛውም አስተዋይና ነፃ አመለካከት ያለው የቴአትሩ ተደራሲ ሊፈርደው የሚችለው ነገር ነውና።

"ሀሁ ወይም ፐፑ" በአፍታ ተፅፎ በአፍታ የሚበን የቾክ ዱቄት አይደለም። ከዘመን ዘመን የማይነጥፍ ኗሪ የብራና ከታብ እንጂ። ከመድረኩ ቁጥር የሚረሳና የሚጠፋም ሳይሆን ዝንተ-በራቂ ህይወት ሕሊና ውስጥ ደምቆ፣ ስሜት ውስጥ ዘልቆ እንደ ፅርሃ-አርያም የሚያበራ ዕድሜያማ መብራት ነው።

አባታችን ባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን

ወቅትን እንተርሰው ብቻ አይደለም "ሀሁ-ፐፑ" የቆጠሩት። የእናትንና የልጅን የተዘበራረቀ አዋይ ነው ያስተካከሉበት። የአንድ ዘመን ሁለት ትወልዶችን ፀብ ነው ያስታረቁበት። በየጉዳናው የምናንኘረቀኘረቀውን ዕንባችንን ነው በመድረክ ቅዱስ መሀረብ ያበሱልን። የአደባባይ ግማት፣ ገልማታችንን፣ የውስጠ-ልባችንን ቅርሻትና ቆሻሻ ነው ሰብስበው እንደእሳት በሚንተገተጉ ቃላቶቻቸው ያቃጠሏቸው። ሃቅን ነው ባለቅኔው በፊደል ያነጠሩት። በቃላት ያነጠቡት።

ታሪክ ቁብ ያልሰጣቸውን፣ የትውልድ ጆሮ እጅግም ያላወቃቸውን በርሃብ የምትስለመለም ሩሃችንን ከርሃብ ጨካኝ ጥፍር ለመንጠቅ እንደመሲህ ደርሰውልን "እውራ ጣት የምታክል ከሰል ስጋ" እስከትቀራቸው ድረስ በአውሮፐላን አደጋ የነደዱትን ታላቁን ባለውለታችንን የሚኪ ሊላንድን ሃውልት ነው "ሀሁ ወይም ፐፑ" ብለው ልባችን ውስጥ ያቆሙት።

ስግብግብ ስሜታችንን፣ ራስ ወዳድነታችንን፣ የዲሞክራሲ ጥማታችንን፣ የአለመከፋፈልና የአለመነጣጠል ፍላጐታችንን ሰንኮፍ አውጥተው ነው መድረክ መቅደሳችን ላይ ያሳዩን። የሚያናቁርና የሚያባላን ደመ-ነፍሳዊ ደዌ በፈረንጅ ሃኪም ሳይሆን በባሕላዊ ዋገምት ነው የፈወሱን ባለቅኔ ፀጋዬ። የቀን ሃሣባችንን ነው ያሳዩን፤ የሌት ሕልማችንን ነው ያስታመሙን። ማንም አሌ ሊለው የማይቻለውን እውነት ነው የዘከሩን።

"ሀሁ ወይም ፐፑ" በረቂቅ የብርሃን ዘገሩ የውስጣችንን ጨለማ ገርቶ፣ ተአምራዊ ፍቅርና ተስፋን ዘርቶብናል። ስለታምና እሳታም ቃላት እንደፈንጅ ፍንጥርጣሪ አካላችንን ሲገምሱን፣ አሳዛኝና አስለቃሽ ቃላት ራሮታችንን ፈንቅለው ሲያስገቡን፣ ራሳችንን ከራሳችን፣ ራሳችንን ከህዝባችንና ከአገራችን ጋር ሲያስታርቁን ነው ያየነው። መድረክ መቅደሳችን ላይ።

ታሪኮን ይህን ህዝባዊ ተቀባሎ ያገኘ ኦሞቀ ሥራ ማንኳሰስና ማንቋሸሽ ለምን? ያሉንን አንጋፋ የጥበብ ቅርስ፣ የምንመካባቸውን የታሪክ፣ የትውልድና የእውነት ምስክር፣ የአባት ባለቅኔ ኦችንን ብዕር ለማኮላሸፍና ለማጨንገፍ ካልሆነ፣ ስብእዊ ክብራቸውን ከፈጠራ ክሊላቸው ጋር ደምሮ ገድሎ፣ የሃቅ እባት የሚተፋ ብዕራቸውን ከሰገባው ለመመሸቅና እሳታቸውን በሞራል ውድቀት ለማስለ ምለም ካልሆነ ይህ የተያዘው ተረባርቦሽ ከቶ ውሉ ምንድን ነው?

ህዝብ ያውቃል። ሕዝብ ይፈርዳል። ህዝብ በትዝብቱ ይናገራል። የሕዝብን ዐይንና ሕሊና በተንኮል ድባል እደብዝዞ የራስን ዲስኩር በሕዝቦች ሕሊና ለመዝራት የሚደረግ የዝና ሽሞ ዛሬ አብቅቶአል።

ዛሬ ፈረጅ መንበር አይደለም። ስም አይደለም። ዛሬ ባለስልጣኑ ስራ ነው። እውነታኛው ምስክር ተግባር ነው፤ ተግባር! እርሱው ብቻ ነው።

" አይችልም መሳደብ "

(ከተስፋዬ ጀምበሬ)

አዋቂን አትንኩ ሊቅ አትናገሩ
ይፃፍበት እንጂ የት ይሂድ ካገሩ
ያልገባው ይጠይቅ ካዋቂ ይረዳ
በኖረበት ምድር አታርጉት እንግዳ
መኖሩ ፀጋነው ባገሪቷ እንብርት
ቢከበር ይሻላል ይቅር አትንካኩት
ዘላለም ያለ ነው አንዱ ካንዱ መብለጥ
በተፈጥሮ ፀጋው ምንድነው ማላገጥ
እስቲ ምን አጠፋ! ለምን ተደፈረ
እጁውን ቀንጭቦ ለሰው ባስተማረ
አሁን ነው ውበቱ በእጃችን ላይ ወርቅ
ከጠፉ በኋላ ምን ያዳርጋል ማድነቅ
እናንተ ብትጠሉት ለኛ ይኑርልን
የሀገር ሀብት ነው ባካችሁ ተዉልን
እርግጥ አይከፋም አይሰጠውም ስሜት
መቼ ይሸበራል ያዋቂ ሰው መንፈስ
ከጥንትም ልክ አለው ባህላዊ ገደብ
ትንሽ ልጅ ታላቁን አይችልም መሳደብ።

ብሔራዊ ሎተሪ NATIONAL LOTTERY

የጐንደሩ አምባቸው 50,000 ብር ደረሳቸው



አቶ አምባቸው ገረመው የደቡብ ጐንደር ነዋሪ ናቸው ። ሙሉ ፈገግታ ተላብሰው ነበር እኛ ዘንድ የመጡት። ጥቅምት 2 ቀን 1985 ወጥቶ ከነበረው ከ659ኛው መደበኛ ሎተሪ ከአንደኛው ዕጣ በሙሉ ቲኬት 50,000 ብር ደርሷቸው ነው። «ሲሰጥ እንዲህ ነው» ይላሉ አቶ አምባቸው ። እየሳቁ - - እየተፍለቀለቁ - - - የሎተሪን በረከት ደጋግመው እያደነቁ - - -

«ባለፈው ዓመት— ከባድ ሥራ ስለነበረብኝ ፣ ብዙ ጊዜ እንደማደርገው ከጐንደር አዲስ አበባ ሳልመጣ ቆይቻለሁ ። የሕህል ውሃ ነገር ጐንደር እቤቱ እሰነበተኝ ። ዘንድሮ ግን ገና በመስከረም አዲስ አበባ መጣሁ ።

«ለካስ የአዲስ አበባዋ የሎተሪ «እድባር» ጠርታኝ ኖሯል ፤ ለ50,000 ብር አሸናፊነት ያበቃችኝን የሎተሪ ቲኬት ከዚሁ ከአዲስ አበባ ነው የገዛሁት» ሲሉ አጫውተውናል ።

አቶ አምባቸው—የሚተዳደሩት በንግድ ሥራ ነው ። ጨርቃ ጨርቅ ይነግዳሉ። በዚያ ላይ አነስተኛ የጭነት መኪና አላቸው ። ሎተሪ ለሌለው ብቻ ሳይሆን ያለውንም ትጐበኛለች ፤ እላማዋም ሳታዳላ ለሌለው ትሰጣለች ላለውም ትጨምራለች ።

በደቡብ ጐንደር ክልል አስተዳደር በእብናት አውራጃ የእብናት ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ አምባቸው ባለትዳርና የበርካታ ቤተሰብ አስተዳዳሪ ናቸው።

«ስንት ልጆች አሉዎት?» አልናቸው ።

«እይለቅበት—ሞልተውኛል ። ስምንት ደርሰዋል ።»

«ገንዘቡን ለምን ተግባር ያውሉታል ?»

«ነጋዴ ደግሞ ገንዘብ አግኝቶ ! ! ! ያው ሥራዬን እስፋፋበታለሁ እንደውም የሳሙናና የዘይት ፋብሪካ የማቋቋም እቅድ ስለአለኝ ለእሱ ተግባር እውለዋለሁ» ብለውናል ።

አቶ አምባቸው «ፈጣሪ የሰጠኝ በረከት ለሰፊው ሕዝብ ይገለጽልኝ» ብለውን ነበር—የተለያየነው ። ታዲያ የእሳቸው የአሸናፊነት ዜና ተራውን ጠብቆ በመገለጫችን እስኪወጣም አላስቻላቸው። « ምነዋ ! ዜናውን አዘገያችሁት ? » ሲሉም ከጐንደር አዲስ አበባ ስልክ ደውለው ጠይቀውናል — እኛም እነሆ ! የድሉን ዜና በእሁኑ መገለጫ አብስረናል ።

ጨዋታ

ለሰው ብሎ ሲያማ ለኔ ብለህ ስማ" (ከወንድሙ ሰንደቅ-ጂማ)

፩ ሥዕላዊ መንደርደሪያ



* የስዕሉ መፍቻ፡-

መ-መርከበኛ
ወ-የ25 ዓመት ወጣት
ዶ-ዶልፊን
ባ-ባህር
ሊ-የ18 አመት ኮረዳ
ጉ-የ35 ዓመት ጉልማሣ

በማድረግ ይመስሏቸው።

፪ ማብራሪያ

እንዲህ ነው፡-በሥዕሉ የሚስተዋሉት ወካዮች በባህር ዳርቻና በባህር ውስጥ የሚኖሩ በልዩ ልዩ ባህርያት የሚመስሉ ተፈጥሮዎች ናቸው። ወዲያና ወዲህ የባህር ሰርጡ ለያይቷቸው የሚታዩትም ጥልቀቱ እንዳይገናኙ ቢወስናቸውም እንዲተያዩ ያስችላቸዋል። እና ሁሉም በእንቅስቃሴ ውስጥ እንዳቸው ሌላቸውን ማስተዋል እንደማይሳናቸው ይገንዘቡ። ዶልፊኑ ደግሞ የሰውን ልጅ ቋንቋ የሚሰማና መናገር የሚችል ፍጥረት አድርገው ይቁጠሩት። መርከበኛውም የባህሩ ብቸኛ አንጓችና ተጠቃሚ። የባህሩ ወሽመጥ እዚያና እዚህ ማዶ ቢጣሩ የሚያሰማ፣ ቢያዩ እይታ የማይከለክል እንደሆነ ማወቅ አለብዎት።

አብዛኛው የፍቅር አጋጣሚ ከአይን አይደል የሚነሳ? "የአይን ፍቅር ብርቱ..." እያለ የዘፈነው ማነው?.....መልከሙ! እና አሻግራ በምትቃኘው የ'ወ' መልከመልካምነት የተነሣ የወዲያ ማዶዋ 'ሴ'የአይን ፍቅር በሚሉት ከፉኛ ትሸናከፋለች። የበረታባት ፍቅር እያየለ ያድርባታል። የወዲህ ማዶው 'ወ' አልተረዳላትም።

ውላ አድራ መውደድ ሲብስባት ይቸግራት ጀመር። በኛ ባህል በደፈናው ሴቶች ባይሞክሩትም 'ሴ' ግን የፀና ነገር ስለፀናባት ተሻግራ 'ወ'ን እንደምትወደው ልትገልፅለትና እሱም እንዲገልፅላት በሃሳብ ተንቆራጠጠች።

አስተውሉ! ያች 'ሴ' ቤሳ ቤስቲን የሌላት ኮረዳ ነች። ግን ፍቅር የያዛት በአይን! የምታፈቅረው ደግሞ ነገሯን ያላጤነላት።

እና የመውደድዋን ዜና ልታበስረው ባህሩን ማቋረጥ ሊኖርባት ነው። በውሳኔው መሠረት አንድ የየብስ አካል ወደሚጋሩትና ቅርቧ ወደሆነው 'መ' ዘንድ ሄደች። በዚያችው ሥራ ወደ ሚተዳደረው አንጓች መርከበኛ ችግርዋን ዘረዘረችለትና 'ምስኪን ስለሆንኩ እርዳኝ' ብላ እንዲያሻግራት ተማፀነችው። ባህር ቀዛፈውን።

'የተለመደውን የማጓጓዣ ኪራይ ካልተቀበልኩ በምን እኖራለሁ?' አለና ንቅንቅ አልል አላት 'መ'።

አሁንም አስተውሉ! ለሚያደርግላት የማጓጓዝ ተግባር ሌላ ውለታ ሥሪልኝ፣ አፀፋ ቁጠሪልኝ አላላትም መርከብ ነጂው። እሱ ለራሱ አስተሳሰቡ ሁሉ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የትራንስፖርቱን ኪራይ ነው ያላት።

ስለሌላት ተስፋ ያጣችው ምስኪን 'ሴ' በአይን ፍቅር ልቧ እየተበላ ወደ ወደብ ቦታዋ ተመለሰች።

በትካዜ እየተንገላታች (ዋሽንት መጫወት ተክናለች) በዋሽንት ከብቸኝነትዋ ጋር ትግል ገጥማ ሳለ'ዶ' ሰማት። ወደ ዳርቻ ቀርቦም ችግርዋን ጠይቆ ሲያበቃ 'እኔ ላሻግርሽ' ነበር ያላት። ለጊዜው የጠየቃት ውለታም አልነበረም።

'ሴ' አማራጭ አልነበራትም ከማይመስላት ፍጥረት ጋር የባህር ጉዞ ማድረጉ ቢያስፈራትም፤ 'ባወጣ ያውጣኝ' ስትል እሣ ነባሪውን (ዶልፊኑን) መሣፈሪያ አድርጋ ባህሩን በሰላም አቋረጠች። 'ወ'ወዳለበትም በደህና ደረሰች። ይህን ስታደርግ 'ጉ' ይከታተላት ኑሯል።

ለ'ወ' የአይን ፍቅር ችግሯን በገለጠችለት ጊዜም 'ሌላ የማፈቅራትና ቃል የገባሁላት ስላለችኝ ይቅርታ፤ ፍቅርሽን ለማስተናገድ እቸገራለሁ' አላት።

በፍቅር ቋንቋ አይሆኑ ሆና ብትለባለስ ብታለቅስበትም "ቃል የእምንት እዳ ነው" ብሎ ዝም 'ወ'።

'ሴ' በ'ወ' ክፉኛ እያ ዘነችበትና መርከበኛውን ከጠላችው በላይ እየተንገሸገሸችበት፣ ሴት ነትዋንም እየተራገመች በዚያው እፍታ እግረ-መንገድዋን 'ጉ' ወ ደሚገኝበት የደሴት ጫፍ በደመነ ፍስ ተጓዘች። አንድ በቀል እየ ታሰባት 'ወ'ን የማስቀናት 'በቀ ል' በውስጧ እየጉነጉነች።

'ጉ' ደግሞ ምን አላት መሰላችሁ?.....'ባጣ ቆይሽን ፈልጊ!' እመጣጥሽን ስከታተል ነ በር። እረማመድሽ ያማልላል። ስከታተልሽ ነበርኩ። እመጣጥሽ አስቀድሞ እኔ ዘንድ ቢሆን ኖሮ ፍቅርሽን ማስተናገድ በወደድኩ ነበር። , ግና መጀመሪያውኑ እኔን ብለሽ ሳይሆን ባህር ያቋረጥሽው 'ወ' ጋ ስለሆነ በምንም መንገድ ልንኳኋን አንችልም። የምረዳሽም ነገር የለም' አላት።

'ሴ' ከሁሉም የሰው ልጆ ች ማግኘት የምትፈልገውን ፍቅርና እርዳታ በማጣቷ በጣም ተበሳጨች። ተፈጥሮንና ሰውንም ረገመች። አ ለመኖርንም መረጠች።

በገጠማት ብሶትና የእድሜ እንቅፋት ተሰነፍንፋ ወደቀች። ከመኖር ወደአለ..ከፍቅር-ፍላጐት -ከሕይወት-ከስሜት....ውጪ በመ ሆን በባህሩ ተዋጠች። ሰጠመች።

እንግዲህ አሁን እርስዎ ለእያንዳንዳቸው ድርጊት በሕሊናዎ ካደረጉት የብይን አሰጣጥ መሰናዶ አኳያ በ'ወ'፣ 'መ'፣ 'ባ'፣ 'ጉ'፣'ደ' 'ሴ' ድርጊት ላይ እንደየጥፋታቸው ፍርድ ይሰጡ ዘንድ ወደ "ሩሕ" የዳኝነት ች ሎት ቀረቡ። በዳኝነት ጀማ ለ"አጥፊዎቹ" የሚሰጡት የብያኔ ሀሣብ ረድፍ ወጥቶለታል። እን በል። (የሞት ፍርድ፣ የእድሜ ልኩ እሥራት፣....እንደሚባለው)

የፍርድ አሰጣጥዎ ተገድ ቧል እንበል፣ ፍትህ ነውና በፍ ትሃዊ አመለካከት በቅዳሚያ አጥፊ ዎቹን ኋላም በነርሱ ቦታ ራስዎን ተክተው በማመዛዘን፣ ከሚከተሉት የፍርድ ሀሣቦች (ከ4ቱ አንዱን ለአንዱ ጥፋተኛ 'ምሱ' ነው ሊሉ ነው።

አቃቤ ችሎቱ ይመዘግባል። ምዝገባው በሰንጠረዥ ይሰፍራል።

የፍርድ አሰጣጥ

(T)-ከበድ ጥፋት ፈፅመ ለሚሉት (Ø)-ዝቅተኛ ጥፋት ፈፅመ ለሚሉት (ነ)-ጥፋቱ አይታየኝም ለሚሉት

ሰንጠረዥ ፩

የአብርሆት ወሳኝ ፊደላት	T	Ø	ነ
መ- (መርከበኛ) ደ- (ደለሌን) ሴ- (ኮረዳዋ) ወ- (የ25 ዓመት ወጣት) ባ- (ባሏ) ጉ- (የ35 ዓመት ጉልማሳ)			

የጥፋት መጠን እስመልከተው በሠንጠረዡ ፍርድዎን በ'X' ምልክት ከሰጡ በኋላ የፍርድ አሰጣጥዎ እርስዎን በግልባጩ እንዴት እንደሚያሳይ ከሠንጠረዥ ፪ ይመልከቱ!

-ሠንጠረዥ ፪ በሚቀጥለው ወር ዕትማችን ይወጣል።

ዘርዓይ ደረስ -(ከገፅ 8 የዞረ)

እንጂ ለህዝብ ፍርድ እንዲቀርብም ተደረገ። በህ ዝቡ ፊት ከተናገረው ንግግር ባጭሩ እንዲህ ይነበ ባል፤

"እኔ ሙሉ ጤነኛ፣ ያለእናንተ በስተቀር ምንም በሽታ የማያውቀኝ የ22 ዓመት ሰው ነኝ። ጥዋት ማታ በየመናፈሻው በየአደባባዩ በየፎቁ ላይ እየሆናችሁ "ሮማ ሮማ ኢጣሊያ ኢጣሊያ" በማለት የምታገኗት አገራችሁ ስለሆነች ነው። ያገርን መውደድ ቋንቋ ካወቃችሁ እኛስ አገራችንን እንድን ጠላ እርስ በርሳችን እንድንጣላ እርስ በርሳችን ተጣልተን መንግስታችንን እንድንረሳ ለምን ታስገድ ዱናላችሁ?

ዛሬ የኢጣሊያንን ወታደሮች ገድለሃል ሕዝ ቡም በአንተ ረብሻ የተነሳ አልቋል። አምድህ በመላ የሮማ ግዛት በነፋስ መበተን አለብህ በሚል ክስ ተከስሼ በዚሁ አደባባይ ቀርቤአለሁ።..... እኔን ለመፋረድ ከሺህ ሕዝብ በላይ እነሆ ተሰ ብስቦ ይታያል። የፋሽስት ወሮበሎች በአገሬ ውስጥ ተሰደው በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሕፃናትና ሽማ ግሌ ጉልማሳና ኮረዳ በጥይት በመርዝ ጢስ፤ በእ ሳት በገደል ባካፉ በዶማ እየተጨፈጨፉ እየተፈለጡ ያለቁት ሁሉ የሚፋረዱት የት ይሆን? የሚፋረዳቸ ውስ ማን ይሆን? ግን የነሱ አጥንትና ደም ዋጋ ሲኖረው የናንተ ስም እየገማ መሄዱን ዛሬ አይታያ ችሁም።

.....አሁንም ለመጨረሻ የምናገረው የኢ ጣሊያ ባንዴራ ይውደቅ፣ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በታላቅ ክብር ትኑር፤ ንጉሥ ተፈሪ በድል አድራጊ ነት ይኑር የይሁዳ አንበሳ ምን ጊዜም ድል ከሱ ይሁን...." በማለት የመጨረሻ የኑዛዜ ቃሉን በሮማ ምድር አሰማ። ከብዙ መሰቃየት በኋላ በተ ወለደ በ29 ዓመቱ ከአምስት አመት እስር በኋላ አረፈ።

ገና ከእነሳሱ "ያለፉት አባቶቻችን አፅም ይሞግተናል" በማለት ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃ ነት ሲፋለም በባዕድ አገር የሞተው ጀግና፤ ከዚ ህች ጉስቋላ አገር ያገኘው ጥቅም ምን ይሆን? እርሱ በህይወት ቢለየን ታሪኩና መንፈሱ ተለይቶ ናል ማለት ነውን? ለማንኛውም እኛም የዘርዓይ ደረስ አፅም እንዳይሞግተን በታሪክ ፊት አስመስ ጋኝ ታሪክ ለማስመዝገብ እንጣር። ጭቅጭቅ ለን ዴት መግባባት ግን ለውጤት የሚያደርስ መሆኑን አ ንዘንጋ። ትላንት ዛሬ ባይሆንም፤ የትላንቱ ታ ሪክ በዛሬው እንቅስቃሴያችንና ተግባራችን ውስጥ የራሱ የሆነ አሻራ አለውና።

ማርጫ -(ከገፅ 20 የዞረ)

ቦች በይበልጥ እየረቀቁ መጥተዋል። በሽታዎች ሆኑ ወይም ሌሎች የሰውን ልጅ በህይወት የሚገጥ ሙትን ችግሮች ለማስወገድ የሚደረጉት ምርምሮች አመርቂ ውጤቶች እያሳዩ ነው። ማርጫ የሰውን ልጅ በህይወቱ ከሚገጥሙት ችግሮች አንዱ ቢሆንም በጣም የሚያሳስብ አይደለም፣ ስለሆነም ማርጫ ሲከ ሰት እንደሕይወት ፍጻሜ ተደርጐ ሳይወሰድ ችግ ሩን ለሐኪም በማስታወቅ መፍትሄ መፈለጉ ይበልጥ ይበጃል።

ከድሮ ጋዜጦቻችን

የኢትዮጵያ ድምፅ ህዳር ፲፪ ቀን 1954 ዓ.ም.

"ሥራ ሥሩ"

(ከጳውሎስ ኞኞ)

የእወጃ መጣፊያዎቻችን ሁሉ ከብዙ ዘመናት በፊት ጀምረው "ሥራ ሥሩ" እያሉ ኖረዋል፤ ይኖራሉም። በእውነቱ ይህን የመሰለ ምክር አይገኝም፤ የመሥራት ትርፍም መበልፀግ ነው። በአባባላቸው በጅተዋል እላለሁ፤ ተዝኪም ነው ብዬ እከላለሁ።

እንደ እውነቱ እናስብ፤ የራሳችን ጉዳይ ነውና እንደራሳችን እንፍረድ፤ "ሥራ ሥሩ" ተገቢ እወጃ ነው። "ምን እንሥራም" መሥመሩን የያዘ ጥያቄ ነው። "ሥራ ሥሩ ሥሩ" የሚሉ ሁሉ፤ እንዴት እንደሚሠራ ማስተማሩ ቀርቶ ዘዴውን አይናገሩም።

ለመሥራት መጀመሪያ መሬት ያስፈልጋል፤ ቀጥሎም ዶማ ቢገኝም አካፋ፤ ቢበለፀግም ትራክተር ያሻል። ሥራ መሥራት፤ ወይንም ማሠራት መሥሪያውን አሟልቶ ነው። ያለ እርሳስ ፃፍ፣ ያለ መፅሐፍ አንብብ ማለት ማስቸገር ነው።

የእወጃው ክፍል "ሥራ ሥሩ" ሲል ሥራ ፈት እየበረከተ መሄዱ የሚያስቅም፤ የሚያሳዝንም ድራማ ይመስላል። ሥራ ፈቱ ሥራ እየጠላ ነውን? አይደለም፤ በጠቅላላው የሚሠራው እያጣ ነው፤ የእለት ሆዱን የሚሞላበት እየተቸገረ ሲፎትግ የሚውለውን ሰው ሥራ ሥራ ቢሉት በምኑ ይቋቋም? በምኑስ ያቀናብረው? በምኑ ተያይዞ፤ በምን ተንጠላጥሎ ሠራተኛ ይሁን?

እንደኔ እንደኔ በሀገራችን አሉ የምንላቸው ሀብታሞች፤ ካላቸው ሀብት እያዋጡ በሀገራችን፤ ኢንዱስትሪዎች ቢያቋቁሙ ቢሞቱ ሀውልታቸው ይሆናል። ሀገራችን ጨሌውንም፤ ቆሎውንም ከውጭ ከመግዛት ድና ኢኮኖሚዋን ታዳብራለች። ሥራ ፈቶች ረሃብተኞች ወንድሞችና እህቶች ሥራ ይዘው ጠግበው ያድራሉ። ሀገራችን ወደ ኋላ ቀረች ማለት እና "ሰነፍ ሕዝብ" እያሉ ማውራት ተገቢ አይደለም።

መንግስትም ቢሆን "ሥራ ሥሩ" ከሚለው እወጃ ጋር የሚሠራው ምንና እንዴት እንደሆነ መግለፅ ይበጃል። በእውነቱ የሥራ ፈቶች ብዛት እንዲቀንስ የሚያስፈልግ የሚሆን ቢሆን፤ ሀገሪቱ ከውጭ በምታገኘው ዕርዳታም ሆነ ብድር የእርሻ መኪናዎች እየተገኙበት በመንግሥቱ ሥራ መሪነት ሥራ ፈቱ ሕዝብ መሥራት አለበት። ያለዚያ ታታሪው ገበሬ በሚያስገኛት ሰብል፤ ወይም ቡና የሀገራችን ኢኮኖሚ እየዳበረ ይሄዳል ማለት ዘበት ነው። የቡናችን ገበያም ዝቅ ማለቱ በዚህ ምክንያት ነው።

ማዕድኖቻችን ቢቻል በግል ሀብታችን፤ ባይቻል ለኩባንያዎች በውል እየተሰጡ ፍላጎቶቻችን እንዲያሟሉ ሆነው ካልተገኙ ባለንበት ይዞታ ላይ እንዳለን ሁነን ጊዜ እያለፈ ጊዜ ሲተካ እኛም እያለፍን ልጆቻችን ይተኩበታል።

(ከመንግስቱ ለማ) (ሎንዶን)

መጣት

New Times and Ethiopia News
February 9,1952

እያ ነጭ አምላኩ ፈጣሪው ፈረንጅ፣
ታሪክ ይሆንና ታዛቢ ፈራጅ፤
የወንዝህ ልጅ ሁኖ ያገርህ ጠበቃ
ተጠየቅ ይልሃል አታውቅ እንደሆነ-
ያሬድ "ዋይ ዜማ" ሲል ዘመረ? ዘፈነ?
ያመ ድጓ ማነው? ድጓስ ማነው?
አባትየው ማነው፣ ማነው ልጅየው?
ኃይለኛው፣ ታላቁ፣ ሥሁል ሚካኤል
ትክክል ፈራጅ ነው፣ ዳኛ ነው ሲባል፤
ለምን አንድ ልጁን ሰደደው ገደል?
"እረኝነት ይሻል ካህን ከመሆን"
ብሎ የተቀኘው ማነው፤ መች፤ ለምን?
ሠረገላ ብርሃን የሚባል ሰው ነበር
የጉጃም ምድር ጉድ የሀበሻ ታምር
እያ ነጭ አምላኩ አልሰማህም እንዴ፣
ያገርህ አርበኛ ዘምቶ ከውጋዴ
መሞቱን ሲወቃ ታንኩን በጉራዴ?
እሡጥ ይህ እንዳልሆን "አለመሰልጠን"
ወይ "በድንቁርና ህይወት ማባከን"
እንደመሠከረ ያ ቴዎድሮስ

ሽጉጡን አጉርሶ ሽጉጡን ሲጉርስ።
እያ ነጭ አምላኩ ተረተሃል አንሣ!
የጣልከው የተውከው ሁኗል መቶ ታምሣ
አንሣ የጣልከውን ያገርህን ዜማ
የሕዝብህን ቋንቋ የዘርህን ግርማ
ያገርህን ጨዋታ ጭፈራ ዘፈን
ያገርህን ልማድ፣ መልካም መልካሙን
እያ ነጭ አምላኩ ምለህ ተፈጠም
አይለምደኝም ብለህ ማጋበሥ መልቀም
ፈረንጅ የጣለውን ያልጣለውንም።
የፈረንጅ ሁሉ ቅዱስ ነው ማለት።
ይውረድ እንደ ወጣ ከራስህ ውርደት።
ሰውነትህን አትካድ ሕዝብህን አትክዳ
አንት ለዘሩ-ባዳ ለሐገሩ-እንግዳ!

> **እርማት**
>
> በ'ፋሕ' ቅፅ1 ቁጥር7 ላይ ከጉሕዴግ ጋር በተደረገው ቃለ-ምልልስ ውስጥ ከገፅ 31 የሶጉሕዴድ ተወካዮች የሚለው የሶዶ ጉርደና ክልል ተወካዮች የጉሕዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ናቸው፤ በገፅ 32 ደግሞ በቀ.ኃ.ሥ. ዘመነ-መንግስት 1934 ሳይሆን 1939 ሆኖ እንዲነበብ እንጠይቃለን።

VARNERO CONSTRUCTION

… HALL - ADDIS ABEBA

HILTON HOTEL - ADDIS ABEBA



MARITIME TRANSIT SERVICES CORPORATION - ADDIS ABEBA



COMMERCIAL BANK OF ETHIOPIA - ADDIS ABEBA

SAHLE SELLASSIE BUILDING - ADDIS ABEBA

ASSAB OIL DEPOTS

AUTOMOTIVE MANUFACTURING CO … ADDIS ABEBA

OUR ADDRESS

VARNERO

Tel. 514511—514318

Fax 511496

Tlx 21193

P. O. Box 3118

ADDIS ABEBA

ETHIOPIA